ያለችውን አነስተኛውን ክፍል ሰጥተውት መኝታውን ዘርግቶ ይኖርባታል ። ለምን እንደመጣ አሰጨንቀው መጠየቁን ባይወዱትም የራሳቸውን ግምት መጣላቸው አልቀረም ። ደም ተቃብቶ በቀል ሸሽቶ ሊሰወር ያቀደ አድርገው ተቀብለውታል ። ነግቶ እስኪመሽ አትክልት ሲንከባከብ ከጉድጓድ ወሀ ሲጎትት አጥር ሲያጠብቅ ፤ ግቢ ሲያጸዳ ይውላል ። ጎንበስ ቀና ባለበት ቦታ ሁሉም ያንጎራጉራል ። ስርቅርቅ የምትል ፉጨቱን አቶ ተገኑም ሆኑ ገብርኤል ይወዱለታል ። ዘወትር ፀኃይ ስታቆለቁል የማታዋን ጨረር ሙቀት ተላብሶ ከበሩ አጠገብ ባደላደለው ሰፊ ድንጋይ ላይ ተቀምጦ ክራሩን ከጭኑ አስደግፎ አሻግሮ የማዶውን ተራራ እየተመለከተ በለሆሳስ ያዜማል ። እንዲህ በሚያደርግበት ሰዓት ማንም በመሀል ገብቶ ቢያናግረው አይወድም ። ቀናም አይመልስም ። ሙሉ በሙሉ በክራር ቅኝቱ ተመስጦ አሻግሮ ከሚመለከተው ተራራ በስተጀርባ ከሚያልመው ዓለም ይሰደዳል። የበጋ የክረምት ልምዱ ስለሆነ ፤ ብርዱ በሚጋገርበት ሐምሌ ነሐሴ እንኳ ካልዘነበ በቀር በዚያች ድንጋይ ላይ ተቀምጦ ክራሩን ሲያከር በቅኝቱ ሲሰወር ይታያል ። አቶ ተገኑም ሆኑ ገብርኤል አፍላ ምሽቱ ላይ የአሰግዴን የክራር ቅኝት ባሉበት ሆነው ካልሰሙ እጅግ ቅር ይላቸዋል ። ቀልባቸው ይሰቀላል ።

አቶ ተገኑ የሚወዱት በዚህ ብቻም አልነበረም ። የተመጠነ ንግግሩንና አደቡን ልበ ሙሉነቱንም ያደንቁታል ። ማስተማር መምከር መተችት የሚወዱት አቶ ተገኑ ፤ የሚናገርም ሰው ማድመጥ ያውቁበታል ። የሚያዳምጡት ንግግር ቁም ነገር የራቀው ከሆነ ግን ተናጋሪውን ቀልቡን ይገፉታል ። ተፈጥሮው የረጋው አሰግዴ ግን አልፎ አልፎ ያልገባውን ከመጠየቅ በቀር ጨዋታቸውን በጥሞና በጨዋነት ያዳምጣል ። ስለዚህም ሀሣባቸውን ለሱ ማካፈል ይወዳሉ ።

ቀድሞ ሲል ምስለኔ ኋላም መምህር የነበሩትና በጡረታ ዕድሜ ላይ የደረሱት አቶ ተገኑ አሰግዴን ፊደል አስቆጥረው ፤ መልካም ሸንሸን ቀሚስ የሚመስለውን ቁምጣ ሱሪውን አስለውጠው ቦላሌ አስታጥቀው ት/ቤት እንዲገባ አባታዊ ተጽዕኖ አድርገው ከጊዜ ወደ ጊዜ ባዩበት ብርታትና ለውጥ ይደሰቱበታል ። እሱም በዚሁ ውለታና ድጋፍ በኑሮአቸው ውስጥ በርካታ አገልግሎት ይሰጣቸዋል ። ለማንም ሳይናገር ጠልቶትና አስመርሮት የነበረው የኑሮው አንዱ ገጽታ ግን የአቶ ተገኑን የእህት ልጅ ምንተስኖትን አንዳንዴም አዝሎ አንዳንዴም ደግፎ ከጠበል ወደ ጠበል መጎተት ፤ ከተኛችበት ማገላበጥ ፤ ጓሮ አድርሶ መመለሱ ነበር ። የአቶ ተገኑን ውለታ የሚመልስበት አድርጎ እየገመተው ሳይወድ ችሎት የተጥመለመለች ሴት ሲያቀና ሲያስተኛ ብዙ ዓመታት አሳልፏል ። ከመልኳ ማስከፋት ሌላ መቆሸሸዋና መጎሳቆልዋ ለሚያያት እንድትቀፍ ያደረጋት ምንቴ ፤ ከብዙ ዓመት ድቀት በኋላ ጥቂት አገግማ በትርና ግድግዳ ተደግፋ ስትንቀሳቀስ ላያት የምትሽመደመድ የምትጎተት ሽባ ትመስል ነበር ። የከሳው ደረቷ ከጀርባዋ ተጣብቆ ጉብጠትዋ ጎልቶ ይታያል ። ከዚህ በላይ ነግቶ እስኪመሽ በአንደበቷ ቃል ስለማይፈጠር እየቀፈፈችም ትከብደው ነበር ።

ከብዙ ዓመታት ሕመምና መኝታዋ በኋላ ግን ጥቂት ለውጥ እየታየባት በመምጣቱ አልፎ አልፎ እደጅ ወጥታ ፀኃይ ስትሞቅ ትታያለች።ከደረቷ ላይ ተጥፈው የሚወዛወዙ አሮጌ እራፊ ጨርቅ የሚመስሉ ጡቶችዋንና ሳይላጭ ብን ብሎ ጠፍቶ ቅሏን ያጋለጠውን ጭንቅላቷን እያከከች እንደ ድንጋይ በተቀመጠችበት ውላ በአሰግዴ

CamScanner

ድጋፍ ትኀባለች ወይ በግድግዳና በምርኩዝ ድጋፍ ትጕ
ተታለች።ወራት እየተዳመሩ ዓመት በዓመት እየተተካ የኋላ
ኋላ እጅግ አዝጋሚ የሆነ የአካል ማገገም ለውጥ እየታየ
ባት መምጣቱን በጥንቃቄ የተከታተለ ቢኖር አሰግዴ ነው።
ህይወት በውስጧ ማንሰራራቱን የተረዳውም አፈርማ የነ
በረው የቆዳዋ መልክ ወዝ እየሰረገው የቀይ ዳማነት ሲታ
ይበት ነበር ። በአቶ ተገኑ ግቢ ከሚያለማው አትክልት
ሌላ ጥቂት ዶሮዎች አሰባስቦ እንቁላል የስጋ ል ሜጩት
የስፈለፍል ነበርና ፤ ለነፍሴ ሲል አንዳንዴ አቶ ተገኑ
ለሳላቸው እንደሚያደርጉት እንቁላል እየመታ ያጠጣት
ነበር ።የምንተስኖት ጉዳይ በአብዛኛው በአሰግዴ ላይ
የተጣለ ኃላፊነት ስለነበር ሙብላትዋን መጠጣትዋን
መተኛት መነሣትዋን ሥራዬ ጉዳዬ ብሎ ተከታትሎ
ይረዳታል ። አንድም ለነፍሱ አንድም የአቶ ተገኑን ውለታ
ለመመለስ ሲል የደረገው የማስታመም ትግል ወደ ኋላ
ተሶፋ እየሰጠው ለምዶትም ጥላቻውና ምሬቱ ቀንሶ ነበር።

በዚየ ደረቅ ሌሊት ምንተስኖት ከሌላኛው ክፍል
ሆና ስታስነጥስ አሰግዴ ከጎን ወደ ጎን እየተገላበጠ የሚ
ያስላስላት በ25 ዓመት እድሜው አግብቷት ዓመት አብ
ሯት ሳይቀመጥ ትቷት የሙጣውን ሚስቱን ነበር ።

ዘመድ አዝማድ ሳይሰናበት የልቡን ምስጢር ለሙ
ሽራ ሚስቱ እንኳን ሳይነግር ሞፈር ቀንበሩን ሰቅሎ ወደ
አዲስ አበባ የኮበለለበትን ዕለት እያሰላሰላት እንደ ተን
ጋለለ እዝን አለ ። ከወዲያ ከወዲህ ተጠራርተው የገና
ዱላቸውን አሾጎርጉረው ወጉና ባህሉ የአገሩም እድር
በፈቀደው ሁኔታ የተጨዋወቱትን የገና ሽኩቻ ረጋ ብሎ
አንድ ባንድ ከጅምሩ እስከ ጭርሱ አሰላሰለው ። የጎነች
ሩር እንደ በረረች መጥታ የመታችውን ስቅጥጥ ብሎ አስ
ታወሰው ከአሥራ ሁለት ዓመት በፊት ከሽኩቻ አምልጣ

ከጉያው ላይ ያረፈች ሩር የፈጠረችበት ህሊናን መሳትና
ሕመም ወዲያው ተሰማውና እጆቹን ከጉየው ላይ አነባ
ብሮ ጭኖ ጉልበቱን እጥፍ አድርጎ ለጥቂት ጊዜ መላ አካ
ሉን ጭብጥ አደረገው ። የዚያች ሩር ጠንቅ በዋለ ባደረ
መጠን ሕመሙን እያጠነከረበት ወንድነቱን እየተፈ
ታተነው በመቸገሩ ካንዴም ሁለቴ እሕል እየጫኑ ትሱና
አባቱ ወደሚያውቁት የአቶ ተገኑ ቤት ተሰዶ መጣ ። እን
ደመጣም ችግሩን ነግሮ የሕክምና እርዳታ ለማግኘት
ስላልደፈረ ምስጢሩን ለብቻው ይዞ ዓመታት ተቀመጠ።

ወትሮም የዘሩ ምሰሶ ተዋቅሮ የነበረው በእርሻ
ሙያ ስለነበረ እዚህም በአቶ ተገኑ ግቢ ጌሾውን ፤ እንሰ
ቱን ፤ ሽንኩርቱን ፤ ቃሪያውን ቲማቲሙን እያለማ እየ
ሸጠ ከዕለት ፍጆታው የተረፈችውን እየቋጠረ አንድ ቀን
ለሐኪም ለሚገልጠው ሕመሙ መታከሚየ ዝግጅት ያደ
ርግ ነበር ። ከጫጩቶቹ መካከል ዳጎስ ያሉትን መርጠ
እንቁላል ለቃቅሞ ከጌሾው ፤ ከእንሰቱ ቆራርጦ ወደ ጉልት
በወረደ ቁጥር ያየውና በኋላም የተዋወቀው አንድ የጉልት
ነጋዴ ከንግዳቸው ባሻገር ሲወያዩ ለሕመም ሁሉ ፋቱን
መድኃኒት መሆኑን የነገረውን የቴትራሳይክሊን እንክብል
እየገዛለት በድፍረት ከመዋጡ በቀር ያደረገው ሌላ ሕክ
ምና አልነበረም ። ከመተኛቱ በፊት በእንጨት ሣጥኑ
ውስጥ ከልብሶቹ ሥር ያስቀመጣትን የአቡጀዲ ከረጢት
አውጥቶ በወገ ሲየሰላ በርከት ያሉ ብሮች እንዳሉትና
ችግሩን ለአቶ ተገኑና ለሐኪም መንገርም እንዳለበት ወሰ
ኖአል ። ለዚህ የገፋፋው ግን ከጥቂት ሳምንታት ወዲህ
መለስ ቀለስ እያለ እየዳሰሰው እየወረረው የሚሠወር ሕይ
ወት ያለው ስሜት ጉዳይ ነበር ።

ይህን እውነታ አምኖ መቀበል እየተሳነው የጥርጣሬ
በሽታ ኳደረበት ሰንብቷል ። የድካሙ ውጤት የሆነውን

የጓሮ አትክልት ተሸክሞ ገበያ በወረደ ቁጥር ከበርካታ ሴቶች ጋር ሲነጋገር ሲከራከር ሲመራረቅ የማያንሰራራው የበደነው ስሜቱ አሁን ፈራ ተባ እያለ እየወረረው መስወሩ አስጨንቆታል ። ለዚህ ስሜቱ ጆሮ ሰጥቶ ያደመጠው የኪዳነ ምሕረት እለት ነበር ። እየተፈራገጡ ፤ እየጮኹ ተጠምቀው የወጡትን በሽተኞች አሳልፎ ከትልቁ ዛፍ ሥር የተቀመጠችውን ምንቴን ልብስዋን አወላልቆ ለአቶ ተገኑ ካቀበለ በኋላ ወደመጠመቂያው ትንሽ ክፍል አቅፎ ደግፎ ሲወስዳት ከምኔውም በተለየ ሁኔታ አካሏ መታደስ እንደ ጀመረ አየው ። ነፍስ ያልተለየው አስከሬን እየመሰለችው ትቀፈው የነበረው ሲለቀው ታውቆታል ። ጠረንዋም አላስከፋውም ።

ከዚያ ወዲህ ሲያስባትም ሲያያትም የአዜኔታም የርኅራኄም እከሌም የማይለው ስሜት ተነባብረው ይጎንጡታል ። በዚያ ደረቅ ሌሊት አቶ ተገኑ በሰጡት ቦንዳ አልጋ ላይ አዲስ የገዛውን የጥጥ ፍራሽ ዘርግቶ አሮጌ ቡልኮውን ከውስጥ አዲሱን ብርድ ልብስ ከላይ ደርቦ ሃሣቡም ልብሱም በፈጠሩት ሙቀት ውስጥ በጀርባው ተንጋሎ መላ ሰውነቱን በተለይም ጉያውን እየደባበሰ ያለ እንቅልፍ እረዥም ሰአት ቆየ።ከነጋ ወዲያ አሸለበው። ምንተስኖት በተለመደው ኑሮዋ ከአልጋዋ ያወረዳት የለም ። አቶ ተገኑም ሲስሉ በማደራቸው በርካታውን ሌሊት ሲሰቃዩ ገፍተውት ስለነበር ንጋቱ ላይ በጣላቸው ከባድ እንቅልፍ እስከ ረፋዱ ተኝተዋል ።

ሳል በሚመላለስባቸው ሰሞን በየማለዳው ሁለት ሁለት የቁብ ዶሮ እንቁላል ከማርና ከለጋ ቅቤ ጋር እየመታ ስለሚሰጣቸው አርፍዶ ቢነሳም ካሉት እንቁላሎች መካከል መራርጦ መትቶ ሊሰጣቸው መነሳታቸውን ለማረጋገጥ ወጣ ገባ እያለ የትልቁን ቤት መስኮት መከፈት

ያጣራል ። ወዲያውኑም በአቶ ተገኑ ሣል ተቀስቅሶ ሌሊቱን ሲያወጣ ሲያወርድ ያደረበትን የጤንነቱን ጉዳይ እንዴት እንደሚነግራቸው ያሰላስላል ።

ከአጥሩ ውጭ ጥቅጥቅ ያለ የኮሽም ተክል ዙሪያውን ተተክሎበታል ። በስተ ግቢ በኩል ደግሞ ተጠጋግቶ የተተከለው የጥድ ዛፍ እርስ በርሱ ተቆራኝቷል ። ከዚያም የአቶ ተገኑ ውሾች ኃይለኞች ስለሆኑ ግቢያቸው የተከበረና የተፈራ ነበር ። አንዳንዴ አትክልት ሊገዙ እርጥብ ጌሾ ሊያስሸመጥጡ ፤ የሚመጡት የአካባቢው ሰዎች እንደ ልብ ወጣ ገባ ብለው አይመላለሱበትም ። ዘወትርም ስለ ሚዘጋ የመጣ ያንኳኳል ውሾችም ያስተጋባሉ ።

አቶ ተገኑ ፤ ያለ ወትሮአቸው ተኝተው ባረፈዱበት የሰንበት ማለዳ የአሰግዴ ወርቁ አቅሉ ተሰቅሎ ወዲያ ወዲህ ሲንጎራደድ የአጥር በር ተቆረቆረና እንግዶች ተከታትለው ገቡ ። ከእንግዶቹ መካከል አሰግዴ ያነጋገረውና የሳመው ወ/ሮ ሙሉን ብቻ ነበር ። በሩን እንደገና በእንጨት ዘግቶ አቶ ተገኑን ለመቀስቀስ አልፏቸው ወደ መኝታ ቤቱ መስኮት ሄደ ። መስኮቱን ደጋግሞ ቆረቆረ ።

በሌሊት ልብሳቸው ላይ የደረቡትን ጋቢ እየጎተቱ መስኮቱን ከፍተው ብቅ ሲሉ ያባበጠው ፊታቸው ከባድ የሕመም ሌሊት ማሳለፋቸውን ይመሰክር ነበር ። ወዲያው መለስ ብለው የእንግዳ መቀበያውን በር ከፍተው እንግዶቻቸውን አስገቡ ። ወ/ሮ ሙሉ ታላቅ ወንድማቸውን ከሳሙ በኋላ አብሯቸው ያለውን ሰው ዘመድ መሆኑን ነግረው አጨባብጠው ካረጀው ሶፋ ላይ ፈንጠር ፈንጠር ብለው ተቀመጡ ።

እህትና ወንድም ስለ ጤናቸው ስለ ኑሮአቸው እየተጠያየቁ ሲወያዩ የመኩሪያ ዓይን ግን አትኩሮ የቀረው

ወደ መኝታ ክፍል በሚወስደው ኮሪደር ላይ ነበር ። ከሁለቱ ሰዎች ንግግር ሌላ ድምፅ ለማጥመድ ጆሮውን ስሎ ተጠባበቀ ።

ከዚያ እርጭና ቅዝቅዝ ካለ ቤት ውስጥ ሌላ ነፍስ አለመኖሩን ከብዙ ቆይታ በኋላ ተረድቶ መንፈሱን አሰባስቦ በሁለቱ ጭውውት ላይ አተኮረ ። ወ/ሮ ሙሉ ሰው አስከትለው የመጡበት ዋነኛ ጉዳይ ነበርና ቢዘገይም አነሱት ።

" ያች ልጅ እንዴት ሆናው ይሆን " አሉ ተስፋ በነጠፈበት አባባል " እግዚአብሔር ይመስገን እሱን ያመነና በእምነቱ የጠና የለመነውን አያጣምና በጎ ነች "አሉ አቶ ተገኑ ዐይኖቻቸውን ወደ መኩሪያ እየወረወሩ ።

" እንዲያው ለመሆኑ ነፍሷን ማወቅ ጀምራ ይሆን"

" እረ ተመስገን ነው ሙሉ ፤ መታዘሏ ቀርቶ በድጋፍ ትወጣለች ትገባለች አንዳንዴም ምርኩዝ ድጋፍ ይዛ መንቀሳቀስ ትሞክራለች እንግዲህ ደግሞ ቀስ በቀስ አንደበትዋ እንዲፈታ ለአምላክ ምን ይሳነዋል ብለሽ ፤ አሉ አቶ ተገኑ የእህታቸውን ጭንቀት ለማጽናናት ብቻ ሳይሆን ሰሞኑን የታዘቡትን የምንተስኖትን ሁኔታ እያሰላሰሉ።

" እሱም ወንድሜ እሷኑ ሊጠይቅ ሁኔታዋን ሊያይ የመጣ ነው" አሉ የዝምድናውን ዓይነት ምን ብለው እንደ ማናገሩ ችግር ብሏቸው ።

" እሱ ማነው" አሉ አቶ ተገኑ ንግግራቸው ከረርና ጎላ እያለ በተቀመጠበት መኩሪያን ከላይ እስከታች እያስተዋሉት ።

" እም " ብለው ወ/ሮ ሙሉ በዝምታ አቀረቀሩ ። አቶ ተገኑ የሚቀበሉትን የአገላለጽ ሁኔታ ወዲያው አስተካክለው ማቅረብ ስላልቻሉ ።

መኩሪያ ቀበል አድርጎ ከምንተስኖት ጋር አብረው የሠሩ እንደ ፤በርና ለረዥም ጊዜ ለትምህርት ጉዳይ በውጭ ቆይቶ ሲመለስ በዚህ እክል ውስጥ መውደቋን ስለሰማ ሊያያት መምጣቱን ገለጹላቸው ። አቶ ተገኑ የግንባራቸው ቆዳ ተሰባስቦ ከረጅም አፍንጫቸው በላይ ሲቋጠር ትርጉሙ ገባውና ወዲያው ቀጠል አድርጎ ዕውቀታቸው ከዚያ ባሻገር ከችግሯ ከመታተምዋ ጋር ምንም ግንኙነት እንደ ሌለው በግልጽ አስረዳቸው ።

ከዚህ በኋላ ወ/ሮ ሙሉ የውዴን ሆስፒታል ገብቶ መውጣትና በወጉ መታከም የመኩሪያንም ልባዊ እርዳታ አንስተው በወንድማቸው ፊት አመሰገኑት ። አቶ ተገኑም አኩብሮት በተሞላው አስተያየት ቁመናውን እየገመገሙ እንደ ወ/ሮ ሙሉ ባይበዛም አመሰገኑት ።

እጃቸውን ሲያጨበጭቡ አስገዴ ወርቁ ፈጥኖ ብቅ አለ ። ምንተስኖት የምትተኛበትን ክፍል እንዲከፍትና አየር እንዲያስገባበት ከነገሩት ጥቂት ጊዜ በኋላ እህታቸውንና መኩሪያን አስከትለው በስተጓሮ ወዳሉት ክፍሎች አመሩ ። የምንተስኖትና ገብርኤሏ መኝታ ክፍል መካከለኛዋ ቤት ነበረችና በርዋም መስኮትዋም ተከፍቶ ጠበቃቸው ። ትራሱንም ጨርቁንም ሰባስቦ አንተርሶአት ስለነበር ቆና ብላ አገኘዋት ። ገብርኤሏ ለእንጀራ ጋገራ ማልደው ወጥተዋል ።

ከከሳው ፊቷ ላይ ወደ ኋላ ሸሽተው በጉድጓዳቸው ውስጥ ከወዲያ ወዲህ በምታንከባልላቸው ዓይኖችዋ ከአንዱ ወደ ሌላኛው ከማየት በስተቀር በአካል እንቅስቃሴ

ወይም እንደበትዋ በፈጠረው ቃል ያሳየችው ያሰማችው ሁኔታ አልነበረም ። ያንኑ በሕመም የጠወለገ አካልዋን እየደባበሱ እየሳሙ ቀርበው ያነጋገሯት ወ/ሮ ሙሉ ብቻ ነበሩ ። መኩሪያ ባየው የአካልዋ ድቀትና ጠቅላላ መለ ወጥ አዝኖ ደንግጦ ጣቶቹን በአፉ ላይ ሸፍኖ ቀስ በቀስ በዐይኖቹ ዙሪያ እንባ እየቋተ ይመለከታት ነበር ። አቶ ተገኑ ግን ከምንጊዜውም ተሽሏታል በሚለው ግምታ ቸው ተበራትተው በፈገግታ ነበር አዘቅዝቀው የሚመለ ከቷት ።

ወ/ሮ ሙሉ ለቅሶአቸውን ዋጥ አድርገው ከአልጋው ላይ ተነስተው ባሻገር ከተዘረጋው አግዳሚ ላይ እንዲ ቀመጥ መኩሪያን ተሸቆጥቁጠው ጠየቁት ። እያዘገመ ሄዶ ከፊት ለፊቷ ቁጭ አለ ። ወ/ሮ ሙሉም ወንድማቸው የነገሯቸውን የመዳን የማገገም ምልክት ለማግኘት አይኖ ቻቸውን ከሷ ላይ ሳያነሱ ዕንባ በሚያረግፈው ዐይናቸው ተመላለሱባት ። ምንተስኖት ግን በፊት ለፊቷም ስላለ ይሁን ምናልባትም በውስጧ ባንሠራራ ስሜት እንያኑ የደከሙ ዐይኖቿን በመኩሪያ ላይ አሳርፋ ለብዙ ጊዜ አስ ተዋለችው ።

አስተያየቷ ስለ በረታበትና ከገባም አንዳች ቃል ስላልተነፈሰ የሙት ሙቱን መንፈሱን አሰባስቦ “ “ እግ ዚአብሔር ይማርሽ ምንቴ ” አላት ወደ ልቅሶ ባደላ አባ ባል፡ ዐይኖቿን ከሱ ላይ ሳታነሣ በአሜንታ አንገትዋን እንደመመለስ አለች ። ወ/ሮ ሙሉ ዘለው ተነስተው ከመ ሬት ሲደፉ ደንግጦ ተነሣ ። መሬቱን ጎንበስ ቀና እያሉ እየሳሙ እጆቻቸውን እያወራጩ ለፈጣሪያቸው ምስጋና ሲያቀርቡ አቶ ተገኑም በተመለከቱት አዲስና ያልተ ጠበቀ ሁኔታ ተነክተው ለአምላካቸው የምስጋና ቃላትን እያነበነቡ በዚያች ጠባብ ቤት መለሰ ቀለስ አሉባት ።

ከአሥራ ሁለት ዓመት ሕመም በኋላ ሰው የሚናገረውን አዳምጣ ተረድታ ምልክት ያሳየችው ያኔ መሆኑን ስለ ነገሩትና እሱንም እንደ ምህረት መልአክ ሊያመልኩት ስለቃጣቸው ወ/ሮ ሙሉን አረጋግቶ እንዲቀመጡ ካደረገ በኋላ ስላለፈ ሕመሟ ምንነት መገመት እንዲችል እን ዴት እንዴት ዓይነት ሁኔታ ይታይባት እንደነበር ቀስ እያለ ጠየቃቸው ። ከአቶ ተገኑም ሆነ ከወ/ሮ ሙሉ ንግ ግር ያጠቃለለው ጭብጥ ግን መብላት አለመብላትዋን ፤ መንጋት መምሸቱን ሳታውቅ ፤ ሰው የሚናገረውን ሳታ ደምጥ ፤ አንድም ቃል ሳትናገር አልፎ አልፎ በሚጥላት ጊዜ አካልዋ ተንቀጥቅጦ ተወራጭታ እንደምትዝል ነበር። ለዚህ ሁሉ ስቃይዋ ሥራዩ ብለው የያዙት መፍትሔ ጠበል መውሰድ እንደ ነበር ና በሕክምና ላይ ተስፋ እን ዳጡም አስረድተውታል ።

መኩሪያ ከዚያች ከምትከብድና በቅራቅንቦ ከተመ ላች ክፍል ሳይወጣ ብዙ ዕቅዶችን ነድፎ የሚወስዳቸ ውን ሙከራዎች በቅደም ተከተል ሳላቸው ። የመኪናው ከጋራዥ መውጣት ወሳኝ መሆኑን ለራሱ አረጋገጧል።

ወ/ሮ ሙሉ ከደስታቸው የተነሣ ምንተስኖት የምትተ ኛበትን ቀዝቃዛ ክፍል ጠረን ለመለወጥና ለማሟሟቅ ሲሉ ነጠላቸውን ወደ ትከሻቸው ላይ ሰባስበው አሰግዴ እቃ ውን ሁሉ እያቀረበላቸው ቡና አፈሉ ። አቶ ተገኑና መኩ ሪያ ስላለፈው ሁኔታዋ ብቻ ሳይሆን ወደፊት ምን ቢደረግ ሊረዳት እንደሚችል ሰፋ ያለ ውይይት ይዘው ቆዩ ። የመ ኩሪያ ትኩረት ያደላው ወደ ሕክምናው ስለነበር ቀስ በቀስ የአቶ ተገኑንም አስተያየት መማረኩ አልቀረም ። አጠ ቃላይ የአካልና በተለይ ደግሞ የአእምሮ ሐኪሞችን ምር መራ በጥንቃቄ መከታተል እንደሚያስፈልግ ደመደሙ። ወ/ሮ ሙሉ ግን ባዩት ባጋጠማቸው ረክተው ፈገግታና

እንባ ከፊታቸው ሳይጠፋ ምንተስኖትን እያዩ ለብቻቸው ያነበንቡ ነበር ። አብሮአት ለረዥም ዘመን የተንገላታ ውም አሰግዴ ወርቁ ፀየው ተስፋ ፈንድ ቋል ። እሱም ዓይ ኖቹን ከሷ ላይ ማንሳት አልሆንልህ ብሎት እያያት ያሰ ፀል በልዩ ልዩ ሁኔታው ውስጥ ይስላታል ።

እንደ ተለመደው አሰግዴ በፈረጠመው ክንዱ አቅ ንቶ በደረቱ ደግፎ ጥቂት ቁርስ ካጎረሳት በኋላ ቡናውን ከአቦሎ እስከ በረካው ሲያጠጣት እሱ እሷን እሷን ፤ እሷ ደግሞ መኩሪያን አትኩረው ይመለከቱ ነበር ። ትናገራ ለች ብለው ሳይሆን ፤ መልስ አገኛለሁ ብለው ሳይሆን እንዲያው አስተያየቷ በመጠንከሩና ከመኩሪያ ላይ ባለ መንቀሉ ፤ " ማን መሆኑን አወቅሽ ?" አሏት አቶ ተገኑ ጭንቀታቸውን ፈገግታ አላብሰው ። ይሄኔም ጭንቅላትዋን እንደማንቀሳቀስ ብላ አዎንታዋን አሳየቻቸው ። የሰው ሁሉ ደስታ ድርብ ሆነ ። መኩሪያም ፊት ለፊት ከተቀመ ጠበት አግዳሚ ወንበር ተነስቶ አልጋው አጠገብ ካለው ድብዳብ ከለበሰው አሮጌ ሳጥን ላይ ተቀምጦ ዐይን ዓይ ኗን እያየ ብዙ ጠያየቃት ። ከአንደበትዋ ቃል ባይወጣም በአካልዋ እንቅስቃሴ የሚናገረውን መረዳትዋን በመ ጠኑ ገለጸችለት ። የመዳንዋን ጉዳይ የጠነከረ ተስፋ አግ ኝተውበት የተመለሱት ግን በስተኋላ ወ/ሮ ሙሉና መኩሪያ ተሰናብተዋት ሲወጡ ካይኖችዋ ጉድጓድ ውስጥ ፈልቀው በወረዱት የዕንባ ፍሳሾች ነው ።

ወ/ሮ ሙሉና መኩሪያ አቶ ተገኑና ምንተስኖትን ተሰናብተው ፤ በቅርቡ እንደሚመጡ ተናግረው ሲወጡ ፤ አሰግዴ ወርቁ ካለማው አትክልቶቹ የቆራረጠላቸውንና የነቀለላቸውን ሰባስቦ በአንድ አሮጌ ዘንቢል ውስጥ አቀ ይቶት ስለ ነበረ እስከ መኪና መሳፈሪያው ድረስ ተሸከ ክሞ ሸኛቸው ። ወ/ሮ ሙሉና መኩሪያ ወደ ፒያሣ

በሚያመራው መኪና ሲለዩት ለመኩሪያ የነበረው አመለካ ከት ጤነኛ አልነበረም ። ማንነቱን በውል ሳያውቅ ፤ ከሱም በጎም ሳይነጋገሩ እንዲያው ብቻ ውቃቤው ጠላው። በልቡ ውስጥ ሲንከላወስ የነበረው ሀሣብ በመኩሪያ ሰበብ የደፈረሰው መስሎ ታየው ።

አሰግዴም አካሄዱን ዝግ አድርጎ አንገቱን አቀር ቅሮ ነገሮችን እንደ ገና እያሰላሰለ አጭሩን መንገድ ዘለግ ያለ ጊዜ ተራመደበት ። ከልቡ ውስጥ ቅሬታ ተሰንቅሮ ህሊናውን ክፉኛ ተጫነው ። የበሰለው የኮሽም ፍሬ ሽታው ከርቀት አውዶት ቆም ብሎ የደከመበትን አጥር በዓይኑ ቃኘው ። ከኮሽሙ ፍሬዎች መካከል ደማቅ ቢጫ የሆነ ችውን አንዱን ቆርጦ እየመጠጠ መለስ አድርጎት የወጣ ውን የግቢ ቆርቆሮ በር ገፋ አድርጎት ገባ ። የግቢውን በር የኋሊት ዘግቶ ወደ ምንተስኖት ክፍል እያዘገመ ሄደ። አቶ ተገኑ ከምንተስኖት አጠገብ ድብደባ ከተነጠፈበት አሮጌ ሣጥን ላይ ተቀምጠው አገኛቸው ።

ከበሩ ፉ ላይ ጥቂት እንደ መቆም ብሎ ወደ ውስጥ ዘልቆ ገብቶ ከምንተስኖት አልጋ ፊት ለፊት ግድግዳውን ተጠግቶ ከተቀመጠው አግዳሚ መቀመጫ ላይ አረፍ አለ። አንደበትዋ ቃል ቢወጣው በሚል አፍ ለማፈታ ሕጻን ንግግር እንደሚያስተምሩ ሁሉ አስቲ ተናገሪ ፤ እስቲ በይው ፤ ሰማሽኝ እያሉ እየደጋገሙ ቢናገሩም እሳቸው ተጨነቁ እሳቸው ደከሙ እንጂ ምንተስኖት እንደ ተመ ኙት ቃል አልተነፈሰችም ። ፈጦ ከወጣው ግንባሯ በታች ከራቀው የዐይኗ ጉድጓድ ውስጥ በድካም የሚንቀሳቀሱ የቦዙ ዓይኖቿን አልፎ አልፎ በዓይኖቻቸው ላይ እያሳ ረፈች አለመቻሏን አቅም ማጣቷን ለማሳወቅ ከመሞከሯ በቀር አፏ አልተንቀሳቀሰም ። ነገር የመገንዘብ አስተያየ ቷን ፤ ቀደም ሲል የታየውን ሁኔታዋን እንደ ብርቱ ተስፋ

ጨብጠው ከመኩሪያ ጋር ያደረጉትን ጭውውት መለስ ብለው አሰቡትና መታከም እንዳለባት ወስነው ከተቀመጡበት ተነሱ ። አሰግዴም ከቅምጡ ተነስቶ ቆመ ።

እነ ወ/ሮ ሙሉ ከሄዱ በኋላ መጥተው ፤ ከመዝጊያው አጠገብ ካለው ምድጃ ምጣዳቸውን አንጋለው ገብርኤሏ ማጂ እሳት ማጫጫስ ጀምረዋል ። አሮጊትዋ ገብርኤሏ ማጂ አጭርና እንደ ጅማት የጠነከረ አካል ያላቸው ደማቅ ጥቁር ሴት ናቸው ። ዕድሜያቸው ከአቶ ተገኑ ዕድሜ ቢበዛ እንጂ እንደማያንስ የሚያውቋቸው ሁሉ ይናገራሉ ። በእርጅና ድካም ግን ከአቶ ተገኑ ተሽለው ይታያሉ ። ከልጅነት እስከ እውቀት በአቶ ተገኑ ኑሮና ሕይወት ውስጥ ጥገኛ ሆነው የኖሩት ገብርኤሏ ሲመቻቸው ሰርተው ሲደክማቸው ትተው ረጅሙን ዘመን አሳልፈውታል ። ከዓመት ልብስ ከእለት ጉርስ የተለየ በውል የታወቀ የወር ደመወዝ የአገልግሎት ክፍያ ከአቶ ተገኑ ተደርጎላቸው አያውቁም ። ለልዩ ልዩ ጉዳያቸው የሚያውሉትን ገንዘብ የሚያገኙት ከአካባቢው መንደር እንጀራ እየጋገሩ ነው። በአብዛኛው ከአቶ ተገኑ ጋር የሚያቃቅራቸው ጉዳይ ደግሞ ካቲካላ መውደዳቸው ነበር ። ይህ የመጠጥ ሱስ ከአንዱ መንደር ወደ ሌላ ሲያንከራትታቸው ስለሚውል ለምንተስኖት የሚገባውን ክትትልና እርዳታ ሊያደርጉላት አልቻሉም ።

በዚህም አቶ ተገኑ ቅር ተሰኝተው ከሳቸው ይልቅ አደራቸውንና ችግራቸውን በአሰግዴ ወርቁ ላይ ጥለው እሱም ጉዳዩ ብሎ ሲያስታምማት ኖሯል ።

የባህር ዛፉ ቅጠልና ቅርፊት እሳት እየደረሰበት ጪሱ እየበረታ ቤቱን ሲያዳርሰው ጪሱን ሸሽተው አቶ ተገኑ ወደ ውጭ ወጡ ። አሰግዴም ተከትሏቸው ወጣ ። ከበራፉ ሲደርስ መለስ ብሎ ምንተስኖትን ከተኛችበት አያት።

እጅዋን እንደማንቀሳቀስ ስታደርግ አደቷት ፊጥኖ ተመለሰ “ ደጅ ላውጣሽ ሲላት በራስዋ እንቅስቃሴ አዎንታዋን ስላሳየችው ልብሷን በቅጡ አለባብሶ ሰብሰብ አድርጎ አቅፎ ወደ ጓሮ አድርሶአት ተመለሰ ። ከሰውነትዋ ማለቅ የተነሣ ቢሸከማትም ቢደግፋትም ችግር ስላልሆነች ካንድ ሥፍራ ወደ ሌላ ሥፍራ በቀላሉ አድርሶ ይመልሳታል ። ወትሮም ቢሆን ችግሩ ከብደትዋ ሳይሆን ይሰበር ይበጠስ የሚመስል የሰለለ አካሏን ለመያዝ መፍራቱና በመኝታ ብዛት ደህና ጠረን የሌለውን ሰውነትዋ ከሰውነቱ አስጠግቶ ማንሳት ማስቀመጡ ይቀፈው ስለነበር ነው ። ከጓሮ መልስ ዘወትር ከሚያስቀምጥበት ሥፍራ የትልቁን ቤት መሠረት አስደግፎ ከደጅ አስቀመጣት ራቅ ብለው የሚሆነውን ሁሉ በአንክሮ የሚመለከቱት አቶ ተጉኑም ንጹህ አየር የፀኃይም ብርሃን ማግኘትዋን ወደዱት ።

እንደ ወይን ተክል ቅርንጫፎቹ ተያይዘው በባላ ተደግፎ ዳስ መስሎ የለመለመውን የጌሾ ተክል ልብ ብለው ሲያዩ ቆይተው ወደዚያው ሲያመሩ አሰግዴ ወርቁም ከኋላቸው ተከትሎ ወደ አትክልቱ ሥፍራ ገባ ። ከትልቁ ቤት ፊት ለፊት ሰፋ ባለው ቦታ ላይ ልዩ ልዩ አትክልትና ቅመማት ተክሎ በቅጠሉም በሥሩም በፍሬውም ጥቅም ማግኘት ከጀመረ ቆይቷል ። ነግቶ እስኪመሽ ሲቆፍር ሲኮተኩት ሲሸመጥጥ ሲገርዝ የአፈሩን የቅጠላ ቅጠሉን ጠረን እንደማገ የልቡንም ስሜት በእንጉርጉሮ እንደ ተነፈሰ ፤ ምኞቱንም በጠነከረ ተስፋ እንዳበረታ የሚውልበት ሥፍራ ነው ። እንኳን ግቢው ከግቢው ውጭ የጥሩ ሽታ ጠረን አየሩን ያውዳል ። ወፎች ቢራቢሮዎች ንቦች ይተሙበታል ። የአካባቢው ነዋሪ እንኳ አመት በዓል ሲደርስ ለጌሾና ለኮባ ቅጠል ብሎ የገበያ መንገድ አይመታውም ። ለምችና ለጉንፋን በሽታ መፈወሻ የሚሆኑ

የአገርኛ ቅጠላ ቅጠሎች ጠይቆ አ.የጣም ። ደማከሴው
ራስ ክምሩ ፤ አረግ ሬሣው ፤ ጤና አዳሙ በአሰግዴ ወርቁ
የአትክልት ቦታ ውስጥ በሚገባ ለምልሟል ።

አቶ ተገኑ አሰግዴን ከቁም ነገራምነቱ ፤ ከጭምት
ነቱም ሌላ በሥራ ወዳድነቱ እጅግ ይወዱታል ። የበለጠ
ስርቶ የተሻለ እንዲጠቀም ፤ ከሁሉም ይልቅ ባለው ጊዜና
አጋጣሚ ሁሉ ለትምህርቱ ቅድሚያ በመስጠት ተስፋ
ሳይቆርጥ ለሩቅና ለጠንከረ ዓላማ ራሱን እንዲያሰናዳ ይመ
ክሩታል ። የተበራከቱለት ዶሮዎች አትክልቱን ጭረው
እንዳያጠፉበት ሽቦ ገዝተው የእንቁላል መጣያ ፤ መዋያና
ማደሪያ ስፍራ ከልለው ካደራጁለትና በመኖ ቀለብ እንዲ
ያረባቸው ካደረጉ ወዲህ ጠቀም ያለ ገንዘብ ማግኘት ጀምሯል ።

አቶ ተገኑ የተቸገረ መርዳትን ያምኑበታል ። እርዳ
ታቸው ግን ለዘለቄታ መፍትሔ ፈር ከማስጨበጥ ጋር ነው።
ሥራ የማይወድ ዘመድም ሆነ ወዳጅ እንዴ በላይ ከሳቸው
እርዳታ ማግኘት አይችልም ።

አቶ ተገኑ አድናቆታቸውን ምክራቸውን እያሰ
ሙት ቲማቲሙን ሽንኩርቱን ድንቹን ቃሪያውን ጎመኑን
እንሰቱን እያዩ አልፈው ወደ ትልቁ ቤት ሲያቀኑ
ጠርቶ አቆማቸው ። መለስ ብለው ሲመለከቱት ጎንበስ
ብሎ አጠገቡ ካለው የጌሾ ተክል ላይ ቀንበጡን እያ
ፍተለተለ ጉዳዩን ጀመረ ። ልብ ብለው አደመጡት ።
ንግግሩን ወደ ማብቃቱ ሲቃረብ ሲያጠራቅመው የኖረ
ውን ገንዘብ ከነከረጢቱ ሰጣቸው ። የተሸመቀቀውን ከረ
ጢት አላልተው ገንዘቡን ካዩ በኋላ መልሰው በጁ ላይ አኖ
ሩለት ።

አሰግዴ በነገራቸው ነገር ሁሉ አጥብቆ ልባቸው በአ
ዘኔታ ቢነካም አጥብቀው ተቆጡት ። እስከ ዛሬ ድረስ
ሕመሙን ሸሽጎ በጭንቀትና በስንኩልነት ስሜት ሲሰ
ቃይ መኖሩን ነቀፉት ። ይህን ችግሩን ሳይውሉ ሳያድሩ
መፍትሔ እንደሚፈልጉለት በአስቸኳይ እንደሚከታተ
ሉለት ሲነግሩት ዝቅ ብሎ እጅ ነሳቸው ። የነገራቸውን
የሕመሙን ጉዳይና የሕክምናውን ዓይነት ግን ከሳቸው
በቀር ሌላ ሰው እንዳያውቅ እያፈረ ለመናቸው ። ልመና
ውን ተቀብለው ቃል ገቡለት ።

በታመመው አካሉ ላይ የሕይወት ስሜት ከመቼ
ጀምሮ በምን ሁኔታና ሳቢያ እንደሚሰማው ሲጠይቁት
ፈጥኖ መልስ ሊሰጣቸው አልቻለም ። ከብዙ ቆይታ በኋላ
ሀፍረት እየተሰማው ጊዜው በቅርቡ መሆኑንና ምክንያ
ቱንና ሰበቡ ግን ከምንተስኖት ጋር የተያያዘ መሆኑን
ገለጹላቸው ። እሱንና ምንተስኖትን በሕሊናቸው ውስጥ
አመላልሰው ካነጻጸሩ በኋላ መልስ ሳይሰጡበት ቀሩ ።
እንዲያው በጥቅሉ ቆይቶ በጀመረው ትምህርት ላይ ጠን
ክሮ እዳር ካደረሰው ያሰበውን የተመኘውን ማድረግ እንደ
ማይሳነው የኪሮሲን አባባል እንደገና ደገሙለት ።

“ ተርበህ አትቅር
ልትበላ ጠንክር
ምጽዋት ግን አትልመድ ”

ኪሮስ የአቶ ተገኑ የት/ቤት ጓደኛቸው የነበረና ካጣ ከነጣ
ቤተሰቡ ርቆ ሸቅሎም ለምኖም የተማረ ከልጅነት እድ
ሜው ጀምሮ ለሥልጣንና ለደረጃ የጣረ ዘወትር ያገሩን
እንጉርጉሮ ለመንፈሱ ሰንቆ ምኞቱን የጨበጠ ብርቱ ሰው
ነበር ። ለምክራቸውና ለማበረታቻቸው ዘወትር የሚጠ
ቅሱትን የኪሮስን ጉዳይ ሲሰማ ይህ የመጀመሪያው ጊዜ

ባይሆንም ምሳሌውንና ምክራቸውን እንደሚከተል ገለ
ጻላቸው ።

ሕክምናውን በተመለከተ ብዙ ከተጨዋወቱ በኋላ
በዚሁ አስታኮ የምንተስኖትን ሁኔታ እንደገና በመጠኑ
እንዲነጋገሩበት አድርገው የመኩሪያንም ማንነትና የዝ
ምድና ደረጃ ጠየቃቸው ። ቀደም ሲል ከአስተያየቱ በመ
ኩሪያ ላይ በጐ ግምት እንዳልጣለ ታዝበውት ስለ ነበረ
የጥያቄውን አቅጣጫ አውቀውታል ። መኩሪያ የሥጋ ዘመ
ዳቸው እንዳልሆነና የምንተስኖት የሥራ ባልደረባ የነበረ
የባዕድ ወዳጅነቱን ነገሩት ። ወዲያውም የምንተስኖትን
ምሁርነትና በሥራ ዓለም ተሰማርታ የነበረች መሆኗን
ነገሩት ። መንገራቸው ፤ የመማር ጥረቱን ሊያገለብቱ፤
በውስጡ እልህና ወኔ ሊረጩ አስበው ነበር ። እስከዚያን
ጊዜ ድረስ ነግረውት የማያውቁትን የምንተስኖትን ማን
ነት ሲሰማ እየተገረመ ከምንጊዜውም የበለጠ አዘነላት።
ወዲያው በአክብሮት መንፈስ አሰላሰላት ። ውስጣዊ
ስሜቱ ግን ሽምቅቅ ሲል ተሰምቶታል ። ለሷ የነበረው
አመለካከትና ግምት ከዚህ የተለየ ነበርና ቸኩሎ የልቡን
ምስጢር ስለ ነገራቸው ቆጨው ። ወደ ኋላ የማይመለስ
በት እፍረት ሆኖ ስለ ተሰማው እሷ ከደረሰችበት ሊደርስ
ለራሱ መሀላ አደረገ ።

በአዳፋዋ ትንሽ ከረጢት ውስጥ የቋጠረውን ገንዘብ
እንደገና እንዲቀበሉትና ለወደፊት የሕክምና ወጪው
እንዲሆን ከሳቸው ዘንድ እንዲቀመጥ ለመናቸው ። አቶ
ተገኑ ማታ ማታ እየተማረ ላጠናከረው ትምህርቱ ማራመጃ
ለልብሱና ለግል ወጪው እንዲሆነው መክረው አልቀ
በል አሉት ። አሰግዴ ወርቁ ማታ ማታ በተከታተለው
ትምህርቱ ሰባተኛ ክፍልን አጠናቆ ወደ ስምንተኛ ተሻ
ግሯል ።

አቶ ተገኑ ወደ ትልቁ ቤት ሲገቡ በጁ የያዘውን ከረ
ጢት ከሰፊ ሱሪው ኪስ ውስጥ ከቶ ምንተስኖት ወደ ተቀ
መጠችበት ታዛ ሄደ ። እኒያኑ የደከሙ ዓይኖችዋን ባንድ
አቅጣጫ ላይ ተክላ አርቃ የምታስብ መስላ ታየችው ።
ከሞላ ጐደል ማንነቷን ከሰማ ወዲያ እንደ እንግዳ ሰው
ልብ ብሎ አስተዋላት ። ቆዳዋ ያሰባሰበውን የእጅና የእግ
ሯን አጥንት በአዘኔታ እያየ ምን ነክቷት ታመመች ፤
ከሕመሟ በፊት ምን ዓይነት ኑሮ ትኖር ኖሯል የሚለውን
የልቡን ጥያቄ እያንከላወሰ በዝምታ ከአጠገቧ፤ብዙ ጊዜ
ተቀመጠ ።

ገብርኤሏ ፤ ከአነጋገራቸው ፤ ካስተያየታቸውም ቢሆን
መቸኮላቸው ይታወቃል ። ነጠቅ ነጠቅ ብለው ተራ
ምደው ወደ ትልቁ ቤት ገብተው ለአቶ ተገኑ የሚበ
ሉት አቅርበው ሲመለሱ ለአሰግዴ ወርቁም የተቻኮለ ትእ
ዛዝ ሰጥተውት ነበር ። ምንተስኖትን ደግፎ አስገብቶ
እንደ ልማዱ በውሀ እያስማገ እንዲያበላትና እሱም ምሳ
ውን እንዲበላ ነበር ።

ገብርኤሏ ማጀ መንደር ውስጥ ላለባቸው ጋገራ ሥራ
የቸኮሉ መሆናቸውን ቢናገሩም ችኮላቸው የሱስ ውጥረ
ታቸውን ለማርገብ እንደሆነ አውቆባቸዋል ። አሰግዴ
ወርቁ ምንተስኖትን ደግፎ ሊያነሳት ቢሞክር በአካል
እንቅስቃሴዋ መቀመጡን እንደ ፈለገችው ስለ ገለጸች
ለት በነበረችበት አስቀምጧት ወደ ክፍሉ ሄደ ። በኪሱ
ይዟት የነበረችውን አዳፋ ከረጢት ከእንጨት ሳንዱቁ
ውስጥ ከልብሶቹ መካከል አርቆ ካስቀመጠና ሳንዱቋንም
ከቦንዳ አልጋው ሥር አርቆ ከገፋት በኋላ ክራሩን ይዞ
ወጣ ። ከበራፉ አጠገብ ካደላደለው ሰፊ ድንጋይ ላይ ተቀ

ምጦ ቅኝቱን ሲጀምር ምንተስኖት መለስ ብላ ከርቀት በቦዙ ዐይኖቿ አየችው ። አሰግዴም እይታዋን በፈገግታ ተቀበለው ። ገብርኤሏ ማጂ ብቻቸውን በምንተስኖትና በሳቸው መኝታ ክፍል ውስጥ እያጉተመተሙ ጥቂት ከጐራረሱ በኋላ የነካቸውን ሊጥ ተለቃልቀው ወጡ ። መብላት ሲያስኛቸው የሚበሉትን የት የት እንዳስቀመጡ ለአሰግዴ ነግረው አልፈዋቸው ወደ በሩ ሲያመሩ እግረ መንገዳቸውን ጤና አዳም ቆራርጠው ያዙ ። ለአፋቸው ጠረን መለወጫ የሚያኝኩት ነበር ።

ምዕራፍ አምስት

እርጅናው የኑሮም ምክርና ትምህርት ተጋግዘው ስለ ገሩት እንጂ የመኩሪያ እናት ወ/ሮ ፋኖሴ እንዲህ እን ዳሁኑ ታጋሽና ገራም አልነበሩም ። ቁጡ ኃይለኛና ደፋር ነበሩ ። የታወቁ የተከበሩ ያደረጋቸው ግን ከዚህ ጋር የማ ይነጠለው የርኅሩኅነት ተፈጥሮአቸው ጭምር ነበር ። ያወቃቸው የተዘመዳቸው ሁሉ እያከበረ ይወዳቸዋል ። ለሰው ችግር ደራሽ ለተጠቃ ጠበቃ ሆነው ትሩፋት ስለ ሚሠሩ ልጁም አዋቂውም ቢፈራቸውም ይወዳቸዋል ። ቆንጥጠውት ያለቀሰ ልጅ ሁሉ ንፍሮ ወይም ቆሎ አፍ ሰው ፤ ዳቦ ገምሰው ስለሚያሸሩት ቂም አይዝባቸውም ። በአጋጣሚ ግጭት ተናግረውት የተቀየመ ተናግሮአቸው ያስቀየማቸው ቢኖር ለችግሩ ጊዜ ቀድመው ደራሽና ለጋስ በመሆናቸው ከወዳጅ ዘመድ ጋር የሻከረ ግንኙነት የላቸ ውም ። ቢቆጡም ቢናገሩም አፋቸው እንጂ ፤ ልባቸው ጭካኔ የለውም ተብሎ በሁሉም ዘንድ ስለ ታመነ ወዳ ጃቸው ብዙ ነው ።

አብረው የኖሩ ቤትና ትዳራቸውን የሚያውቁት ጐረ ቤቶችና ቤተ ዘመዶች እንደሚያወሩት ወ/ሮ ፋኖሴ ለመ ኩሪያ አባት ሚስት ሆነው በሞት እስኪለዩዋቸው ድረስ ሊቆዩ የቻሉት በኃይለኝነታቸው መሆኑን ይናገሩላቸዋል።

ረዘም ባለው ቁመናቸው ለቀቅ ብሎ በሚታየው ሽንጣቸው ላይ ድጋቸውን አዙረው ዝናራቸውን ታጥቀው ጉፈሬያቸውን ብን አርገው አበጥረው ጽዱ እጀ ጠባብ ሱሪያቸውን ታጥቀው ብቅ ያሉ ጊዜ የብዙ ሴቶችን ልብ ያስሸፍቱ የነበረት የመኩሩያ አባት ፤ በዚሁ ፤ ቁመናቸውና ሁኔታቸው ወ/ሮ ፋኖሴን ከባላቸው ላይ አስኮብልለው አግብተዋቸዋል ። ቅብጥብጥና ወረተኛ የነበሩት የመኩሪያ አባት ቢበዛ አንድ ዓመት አለዚያ ለመንፈቅ ያስቀመጧትን ሴት አስደግሰው ለሌላይቱ ሴት መቀበያ አዘጋጅተው ነባርዋን ይፈቱ ነበር ። ወ/ሮ ፋኖሴ ከዓመት ቆይታቸው በኋላ በስለትና በዝክር ስም ድግስ እንዲደግሱ ሆኖ የኋላ ኋላ ጥርጣሬ ስላደረባቸው የተመረገውን የጠላውንና የጠጁን ጋን ሰብረው የተቦካውን ደፍተው በጠፍ ጨረቃ ወደ ዘመዶቻቸው ይሸሻሉ ። ይህን ያዩ የመኩሪያ አባት በድፍረታቸውና በልበ ሙሉነታቸው ይልቁንም ስለ ወደዷቸው እንደገና አማላጅ ልከው ተመልሰው እንዲገቡ ከሆነ በኋላ እስኪሞቱ ድረስ ሚስትና ጓደኛ ሆነዋል ይላሉ ። የበስተኋላውን አደባቸውንና ትዕግስታቸውን ዘመድም ሆነ ባዕድ በመደነቅ ይመለከተዋል ።

ወ/ሮ ፋኖሴ ሥጋና እርጅና የተጫነውን አካላቸውን እየጐተቱ ሄደው ከሆስፒታል በር ላይ ተንቅቅተው ከተመለሱ ወዲህ ባዩትና በሰሙት ሁኔታ ቅር ተሰኝተው በተለይም የወ/ሮ ሙሉን የልጅ እናትነት ጠይቀው ከተረዱ በኋላ በመኩሪያ ተቆጥተው የምር አኩርፈውት ልጅቷን ጳነች ወይስ ሞተች ሳይሉት ቀርተዋል ። ከዚያም ወዲህ የተናገሩ በጐም ሆነ ክፉ ቃል አልነበረም ። እንደወትሮው ቢሆን ቅሬታቸው በዝምታ አይወሰንም ነበር ።

መኩሪያም ወ/ሮ ሙሉን አስቁመው ካነጋገሩ በኋላ የሚኖራቸውን የተሳሳተ ግንዛቤ አውቆ በወቅቱ ከልቡ ስቋል ። በዝምታቸው የሸሹትም በዚሁ ምክንያት እንደሆነ ገብቶታል ። ሊያስረዳቸው እያሰበ በቀላሉ የማይመለሱ በመሆኑ የልብ ጓደኛቸውን እማሆይ ሻሸቱን ይዞ እውነተኛውን ሁኔታ ሊነግራቸው አቅዷል ። ጊዜ እያጠረው ያሰበውን ባለማድረጉ በሱና በእናቱ መካከል ንግግር ከተቋረጠ ቆየ ። ቢያመሽም ቢቀርም መጨነቃቸውን ችለው እያለፉት መቆጣታቸውንና መጠየቃቸውን ትተውታል ።

እማሆይ ሻሸቱን ይዞ ለመሄድ ባሰበበት ቀን ሌላም እቅድ ስለነበረው ቅድሚያ ለእቃ ሸመታው አደረገ ። ለሴት የሚሆን ልብስ ገዝቶ ስለማያውቅ የሚያጋዛው ሰው እንደሚያስፈልገው በመረዳት ሲያሰላስል ቆይቶ ከሚያውቃቸው ሴቶች ሁሉ ትሻላለች ብሎ መረጣት ። የዓመት ፈቃዱን ወስዶ የቢሮ ውን ሁኔታ በወግ በወጉ ከውና ለሃያ አምስት ቀናት ከመስሪያ ቤቱ ሊለይ ከሥራ ሰዓት በኋላ ሲወጣ በቀጥታ የሄደው ወደ ፋናዬ ቤት ነበር ።እንደደረሰ አላገኛትም ። መጠበቁ ጊዜውን ስላባከነበት ሀሳቡን ለውጦ ወደ አፍንጮ በር መኪናውን አበረረ ። ውዴን ይዞ ወደ መርካቶ ተሻገረ ። የውስጥና የላይ የሚሆኑ ልዩ ልዩ ልብሶችን ጋቢና ነጠላም ጭምር ሻሽና ቅባትም ሳይቀር ገዝተው ለዐይን ሲይዝ ጉለሌ ከነአቶ ተገኑ መንደር መኩሪያና ውዴ ደረሱ ። ለማግስቱ የሀኪም ቤት ጉዞ ምንተስኖትን እንዲያዘጋጅዋት ካሳሰባቸው በኋላ ውዴን ይዞ ተመለሰ ። አፍንጮ በር አፋፍ ላይ አድርሶአት እስክትወርድ ድረስ በጠየቀችው አንዳንድ አስደንጋጭ ጥያቄ ተወጥሮ ራስ ምታት ጀምሮት ነበር ። ጃንሜዳን በስተግራው ትቶ በኪዳነ ምህረት ት/ ቤት በኩል ቁልቁል ወርዶ

ቀበናን ተሻግሮ ወደ ሾላ መስመር ቀስ እያለ እያሽከረከረ ተጓዘ ። ኮመንደሪ ደርሶ ዳግመኛ ቤቷን ቢያንኳኳ ፋናዬ አልነበረችም ። ቅር እንዳለው ተመልሶ ወደ እቴጌ ሆቴል አመራ ። አገኛት ይሆናል የሚል የደበዘዘ ተስፋ ነበረው። ቢራ አዞ ከተቀመጠ በኋላ በያቅጣጫው በዓይኑ ፈልጎ ስላጣት የሷን ነገር ትቶ በወሰዳቸው የእረፍት ቀናት የሚያደርገውን ሁሉ በመልክ በመልኩ በቅደም ተከተል መንደፍ ጀመረ ።

እንደ ወትሮው እቴጌ ሆቴል ብዙ ሊቆይ አልቻለም። ወደ ቤቱ ተመልሶ በጊዜ ራቱን በልቶ ተኛ ። ከንጋቱ 11 ሰዓት ላይ ከመኝታው ተነስቶ ከለባበሰ በኋላ ሠራተኛዋን ከመኝታዋ ቀስቅሶ ለሥራ ጉዳይ መሄዱን ነግሯት ወጣ ። ባያናግሩትም መጨነቃቸውን ስለሚያውቅ መልእክቱን ለእናቱ እንድታደርስ አስቦ ነበር መናገሩም ።

ከፓስተር ኢንስቲትዩት አጥር ጋር የሚካለለውን የአቧራ መንገድ ይዞ ወደ ውስጥ ራቅ ወዳሉት መንደሮች ገባ ። ከየትኛውም ሥፍራ ይበልጥ ብርድና ቅዝቃዜ ፀሀር ዛፍ በበዛበት በጉለሌ አካባቢ ስለሚከብድ ለዚሁ ሲል መኩሪያ ጋቢ ለብሷል ። ቅዝቃዜው ተጋግሯል ። ንጋት የሚያባርራቸው ጅቦች ድምጻቸው ከርቀት ይሰማል ። ውሾችም ከያሉበት አኮታትለው ይጮኻሉ ። በኮሽምና በጽድ ተክል ግጥም ብሎ ከደረጀው የአቶ ተገኑ አጥር ደርሶ የመኪናውን ሞተር ሲያጠፋ የግቢው ውሾች ተንገብግበው ጮኹ ። ወዲያውም አሰግዴ ወርቁ የአጥሩን በር ከፈተና ብቅ አለ ። አዲስ የገዛውን ብርድ ልብስ ተጐናጥፎ ነበር ። የጠዋት ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ተከታትለው ገቡ ። አቶ ተገኑና ገብርኤሏ ከምንተስኖት አጠገብ ተቀምጠዋል ። ጊዜ ቢወስድባቸውም ምንተስኖትን አለባብሰውና ሸፍነው ካዘጋጁዋት በኋላ አሰግዴ ወርቁ

ደግፎ እያራመዷት ወደ መኪናው ወሰዷት ። ከኋለኛው መቀመጫ አሰግዴ ደግፏት ሲቀመጥ አቶ ተገኑ ደግሞ ከመኩሪያ አጠገብ ተቀምጠው ወደ ዘውዲቱ ሆስፒታል ተጓዙ ። ከሆስፒታሉ ቅጥር ግቢ ገብተው ሕሙማንና አስታማሚዎች ተኮልኩለው ወደሚታዩበት ሥፍራ አመሩ ። ሌሎቹን እንዳይወርዱ ነግሮ መኪናውን ጥግ አስይዞ አቁሞ መኩሪያ ቁጥር ሊቀበል ቁጥር ወደሚሰጠው ሠራተኛ ዘንድ ሄደ ። ሰዓቱ ገና አስራ ሁለት ሰዓት ከሃያ ነበር ። ለዕለቱ የተወሰነው ቁጥር ማለቁን ሲሰማ ደነገጠ ። አስተዛዝኖ ለመንገርም ቢሞክር ቁጥር ሰጪው ሠራተኛ ጭራሽ አመነጫጨቀው ። ከሆስፒታል ዘበኞችና የአገልግሎት ሠራተኞች ጋር ኮከቡ ለምን አልገጥም እንዳለው እያሰላሰለ ተበሳጨ ። ኩዚያ ተመልሶ አንዴ ካርድ ክፍል አንዴ ድንገተኛ ክፍል እየተመላለሰ ችግሩን ለማስረዳት ቢሞክርም ቁጥር ካልያዘ በቀር ሊረዱት ቀርቶ ሊያዳምጡት እንደማይፈልጉ በሁኔታቸው ተረዳና በብስጭት እየተሳደበ ተመለሰ ። “ ጋሽ . . . ጋሽ . . ” የሚል ጥሪ ሲሰማ ወደኋላው ዞሮ ወደሱ የምትመጣውን ጋቢ በረጅሙ የለበሰችውን ሴት ቆሞ ጠበቃት ። ፋናዬ ነበረች ። በአጠራርዋም ተገርሞ ሳቀ ። የፈለገውን ጠይቃው ፈጥና ወደ ቁጥር ሰጪው ተመለሰች ። ከመኪናው ውስጥ ተቀምጦ ጠበቃት ። ብዙም ሳትቆይ የሕክምና ተራ ቁጥሩን ይዛለት መጣች ። አምስት ቁጥር ይል ነበር ።

ቁጥሩን ከሰጠችው በኋላም ሀኪሞቹ ሲገቡ ልትረዳው ስላሰበች ሥራ ላይ ያደረችው ፋናዬ አብራው አረፈደች ። የጉዳዩ ባለቤት መኩሪያ ብቻ መሆኑ ቀርቶ ፋናዬም ሆነች ። ሲስተር ፋናዬ ከወዲያ ወዲህ በምታውቀው አሰራር ተሯሩጣ ምርመራው ተጠናቆ ለምንቴ የመኝታ ህክምና ተፈቀደና ተኛች ። እነ መኩሪያ ከመድረሳቸው

በፊት ደርሰው ብርድ ላይ ተኮልኩለው ቁጥር የያዙት ሕመምተኞች ተሶልፈው እንደ ተቀመጡ እነ መኩሪያ ጉዳያቸው መልክ ያዘ ። ምንም እንኳ ችግራቸው መፍትሔ ቢያገኝና ምን ተስኖትም ለሙሉ ሕክምና እርዳታ መተኛቷ ቢያስደስታቸውም በዘመድ ድጋፍ ባገኙት ቅድሚያ አገልግሎት መኩሪያም ሆነ አቶ ተገኑ ቅር ተሰኝተው በብርድ ተጨብጦ በሕመሙ እየተሰቃዬ በዝምታ የሚመለከታቸውን ሰው ቀና ብለው ለማየት አፈሩ ። ተራ ይዘው ሲጠብቁ የነበሩት በሽተኞችም ሆኑ አስታማሚዎች ከመታዘብና ከማጉረምረም በቀር ገፍተው ሊቃወሙ አልሞከሩም ። ከጊዜ ጊዜ የጠነከረ በአንደበትና በመመሪያ ደረጃ የሚወገዝ አሰራር መሆኑን ያመኑና ቢጋፉም ትርፉ የህክምና አገልግሎት እንዳያገኙ ወይም ቀና አገልግሎት እንዳያጡ የሚያደርጋቸው አድርገው የገመቱት ይመስላል ፤ እንዲያው ዝም ብለው አድራጎቱን ታዘቡ ።

ይህን ሁኔታ ልብ ያላለውና ግድም ያልሰጠው አሰግዴ ወርቁ ነበር ። የሱ ትኩረቱ ሁሉ ያረፈው በምንተስኖት ምርመራ ላይ ሆኖ በአልጋ ላይ ዘርግተዋት ካንዱ ክፍል ወደ ሌላው ሲጐትቷት የሞተች ያህል አዘን ገብቶት እየተከተለ ያያት ነበር ።

ከዚያ ወዲያ ለአዳሩና ለውሎው የማስታመም ተረኛነት አቶ ተገኑና አሰግዴ ሲቀሩ በቀር ወ/ሮሙሉ ውዴ መኩሪያና ፋናዬ ተራ ገብተው እየዋሉ እያደሩ ከምንተስኖት አጠገብ ሳይለዩ አስታመሟት ፡ ከዕለት ዕለት መሻሻል መጠንከርና ፈጣን የአካል ማገገም እያደረገች ብትታይም የመናገርዋ ነገር ግን ምንም ምልክት ሳይገኝበት ቆየ ። ከሰውነቷ መታደስ ጋር የማስታወስና የመገንዘብ ችሎታዋ እንደሚያንሠራራ ያረጋገጡት ሀኪሞች ርኅ

ራሄ የተሞላው የሕክምና ክትትል እያደረጉላት የዕለት ዕለት ለውጧን በጥንቃቄ ይከታተሉ ጀመር ።

ሕሙማን በሚጠየቁበት ቀናት የሚመጡት ቤተ ዘመዶች ጐረቤቶች ልሣንዋ ባይፈታም የአካልዋን መታደስ እንደገና የመፈጠር ያህል መሆኑን እያደነቁ ይመለሳሉ ። የመንፈስ ደስታ ስለ ተሰማቸው ይመስላል ወ/ሮ ሙሉም በዚሁ ጊዜ ውስጥ ወዛቸው ተመልሶ ረጋ ብለው ታይተዋል የቅርቡም የሩቁም ዘመድና ጐረቤት እንዳቅሙ እንደ ቅርበቱ እንጀራ በሣህን ቋጥሮ እንዳዲስ በሽተኛ በወጉ ጠየቃት ። ባንዱ ሰንበት የሕሙማን መጠየቂያ ዕለት ጠያቂዎቿና አስታማሚዎቿ እንደ ተሰበሰቡ እንደተለመደው ዐይኖቿን ከሰው ወደ ሰው እያመላለሰች ቆይታ ጥቂት እንደ ማሸለብ ሲያደርጋት የደራ ወሬ በጥንድ በጥንድ የያዙት ሁሉ ከክፍሉ ወጣ ብለው እንዲጨዋወቱ ተነጋግረው ሲወጡ አሰግዴ ብቻ በስተግርጌዋ ካለው የአልጋ ጠርዝ ተደግፎ እንደ ቆመ ቀረ ።

ዐይኗን እንደ ከደነች የግንባሯን መቋጠርና መፈታት የደም ሥሮቿን መፍጠጥ በፊቷ ላይ እየተመለከተ የወትሮውንና የቅርቡንም ገጽታዋን ሰውነትዋን እያወዳደረ እየተደነቀ እየተደመመ ሳለ ከጭንቀት ባንና እንደ ተነሳች ሁሉ ዐይኖቿን በሰፊው ከፍታ ዙሪያዋን በችኮላ ማየት ስትጀምር በቆመበት የድንጋጤ ውጋት ያዘው ። መለስ ቀለስ ብላ ዙሪያዋን ደጋግማ ከማተረች በኋላ በአሰግዴ ላይ ስታፈጥበት ከተደገፈው አልጋ ጥቂት እልፍ ብሎ ቆመ ። ከተንጋለለችበት ቀልጠፍ ብላ ቀና ብላ የአልጋውን ጠርዝ በእጆችዋ ጨብጣ አንገቷን ወደሱ ስታሰግበት ወደ ኋላው እንደ መሸሽ ቃጣው ። “ ልጄ ስ” ስትለው በሰማው ቃልና ያልተለመደ አንደበት ደንግጦ በሩን ከፍቶ ተንደርድሮ ወጣ ። ሁኔታውን ያዩ በበረን

CamScanner

ዳው ላይ ሲጫወቱ የነበሩ ዘመዶችዋና ጠያቂዎቿ ሁሉ እየተጋፉ ሲገቡ ፡፡ ከተኛችበት ተነስታ አልጋውን ላይ ተደላድላ ተቀምጣ ሰውነቷ እየተንቀጠቀጠ አፍጥጣ አገኟት ፡፡

ሁሉም ሊጠጋት ፈርቶ አልጋዋን ከቦ ቆመ ፡፡ ወ/ሮ ሙሉ አለፍ ብለው ትከሻዋን እንደ መያዝ ካደረጉ በኋላ "ምነው ምንትዬ ምነው እናቴ" አሏት በሚያባብል ጥያቄ ፤ የቆሙትን ሁሉ ተራ በተራ ካየች በኋላ አፏን ከፈት ዘጋ ከፈት ዘጋ አድርጋ አሁንም ደግማ "ልጄስ" አለች ፡፡ ይኼኔ ወ/ሮ ሙሉ እልልታቸውን አቀለጡት ፡፡ ጐረቤቶቻቸውም እንደ ጨሌው ቀን ትብብር እልልታውን ተቀበሏቸው ፡፡ በክፍሉ ውስጥ የነበረው ሁሉ ምን ተስኖትን እየተቀባበለ ሳማት እርስ በርስም እየተሳሳሙ ደስታ የፈነቀሉው እንባቸውን አፈሰሱ ፡፡ እልልታውና ጫጫታው የአካባቢውን ሕሙማን በማወኩ የምንቴን ጠያቂዎች የሀኪም ቤቱ አስተናባሪዎች እየገፉና እየመነጫጨቁ አስወጧቸው ፡፡ ያዩት ሁኔታ ያስገረማቸውና ያስደነቃቸው ስለ ነበረ እንግልቱ አልተሰማቸውም ፡፡ ወዲያው ሁኔታው የተነገራቸው ሀኪሞች ተከታትለው ሲገቡ ዘመዶችዋ ለጥቂት ጊዜ እውጭ እንዲቆዩ ተነገራቸውና ሀኪሞቹ በር ዘግተው ምርመራቸውን ቀጠሉ ፡፡ ወ/ሮ ሙሉ የደስታ ዕንባ ሲያነቡ ነበር ጐረቤቶቻቸውም አለቀሱ ደስታ እየፈነቀለው የተዋጣው ዕንባ ከነስሜቱ የሚያስገርም ነበር ፡፡

የልብ ምትዋን የአካል ሙቀትዋን የደም ግፊትዋን ከመረመሩ በኋላ የቃል ጥያቄ ተራ በተራ አቀረቡላት ፡፡ መልስዋ ፈጣን ባይሆንም በቀስታ ለተጠየቀችው ሁሉ የአግባቡን መልስ ሰጠቻቸው ፡፡ የተለያየ ምርመራ ያደረጉላት አራቱም ሀኪሞች ደስታና እፎይታ ታየባቸው፡፡ ግንዛቤዋንና የማስታወስ ችሎታዋን ለመፈተሽ ሲሉ

በአካባቢው ያለውን ምኑንም ምኑንም ዕቃ ይኼ ምንድነው ፤ ምን ይባላል ፤ ለምን ይጠቅማል እያሉ እያጨዋወቱ ሲጠይቋት የሳተችው ነገር አልነበረም ፡፡ የኋላ ኋላ የሷ ጥያቄ ግን "ልጄስ" ነበር ፡፡

ከዶክተሮቹ መካከል የነርቭ ሕመም ሀኪም የሆኑት ደርባባ ሰው ወደ ውጭ ብቅ ብለው "የምንተስኖት ልጅ የታለች ወዲህ ትምጣ" ሲሉ በረንዳው ላይ ቆመው ደስታና ድንጋጤ የሚያቅበጠብጣቸው ቤተ ዘመዶች አንዱ ሌላውን ከማየት በቀር በሩን በመጠኑ ከፍተው አንገታቸውን ብቅ ላደረጉት ዶክተር መልስ የሚሰጣቸው ጠፋ ፡፡ ከጥቂት ቆይታ በኋላ አቶ ተገኑ ከአጠገባቸው የቆመችውን ውዴን ትከሻዋን ያዝ አድርገው ወደፊት ካራመዱዋት በኋላ ለዶክተሩ አቀረቡዋት ፡፡ ውዴ በፍርሃትና በድንጋጤ ተይዛ ነበርና ለመግባት አመነታች ፡፡ ወዲያው መኩሪያ ወደ ጆሮዋ ጠጋ ብሎ ሹክ ካላት በኋላ ዶክተሩን ተከትላ ገባች። አላስችል አለውና መኩሪያም ተከትሎ ገባ።

በጥያቄዋ መሠረት ሀኪሙ ውዴን ሲያቀርቡላት እጆችዋን ይዛ በውል ካስተዋለች በኋላ የውዴን አንገት አንገቷ ስር አስገብታ ስቅስቅ ብላ ስታለቅስ ጸጉርዋንም ፊቷንም እጅዋንም እያገላበጠች ስትስም ሀኪሞቹ በአዘኔታና በደስታ በእርጋታ ሲያስተውሉ መኩሪያ ግን ጥግ ይዞ ያለቅስ ነበር ፡፡ ዕረፍት እንድታደርግ መክረው ትራስዋን አደላድለው እንድትተኛ ሲያደርጉ አሻግራ ግድግዳ ተደግፎ የሚያለቅሰውን መኩሪያን አይታ እንደገና ተነሣች ፡፡ ስሙን ጠርታ እንዲቀርባት ከጠየቀችው በኋላ እሱንም በሰቀቀን ሳመችው ፡፡ ሳማት ፡፡ በዚያ ቀን በርካታ የደስታ ዕንባ በዚያ ክፍል ፈሰሰ ፡፡ እያነቡ ደስታ ሆነ ፡፡

ደንብሮ እንደወጣ አንድ የበረንዳ ቋሚ ተደግፎ የቀረው አስግዴ ወርቁ ያስደነበረው ድንገት መናገርዋና ከመ

ናገርዋም ባለልጅ መሆንዋን በገዛ አንደበቷ መስማቱ ጭምር ነበር ። የምንተስኖት ልጅ ተብላ ውዴ በመግባቷ ለናፍቆት ማስታገሻነት በምትክነት ያቀረቡላት እንጂ መቼውንም ውዴ የምንተስኖት ልጅ እንዳልሆነች በልቡ አምኗል ። ሌላ ልጅ አታጣም ብሎ ግን ጠረጠረ ። ሀኪሞቹ ሲወጡ ግርግሩ ረጋ ሲል አሰግዴም ገብቶ ቆመ ። የግንባራቸውን ወዝ በኩታቸው ጫፍ ጠራርገው በተኛች በት ግንባሯን እንደገና አቶ ተገኑ ሳሟት ። ትኩሳትዋ ለከንፈራቸው ተሰምቶታል ። ገጽታዋ ላይ ፈገግታ ተነጥፏል። በግራ እጅዋ አልጋው ላይ ጠልጠል ብላ የተቀመጠችውን ውዴን እንደያዘች ዐይኖችዋን ከደን አድርጋ ቆየች ። የሁሉም ዐይን በሷ ላይ አርፎ እንቅስቃሴዋን ለማየት ቃልዋን ደግሞ ለመስማት ተጠንቅቆ ይጠብቃታል ። ድካም ይሁን ሀሳብ የተጫናት በውል ባይታወቅም በዝምታ እንደ ተጋደመች ውዴን እንደ ጨበጠች ጥቂት ጊዜ አለፈ ከሁሉም መኩሪያ እጅግ ተደሰተ ሙሉ ፈቃዱን ጊዜውን ገንዘቡን የሰዋለት የምንተስኖት ጤና በመስተካከሉ ደጋግሞ አምላክን አመሰገነ ።

ወ/ሮ ሙሉ የመኩሪያን ጭንቅላት ወደሳቸው ቁመት ዝቅ አድርገው ግንባሩንም ጉንጩንም አንገቱን ጸጉሩንም ከሳሙት በኋላ ሲስተር ፋናዬንም ባልተናነሰ ሁኔታ እቅፍ አድርገው ሳሟት ። በሰው ድጋፍና ሸክም የገባችው ምንተስኖት እንደገና የተፈጠረ ሌላ ሰው ሆና ራስዋን ችላ ስትራመድ ስትናገር ያዩ የሰሙ ሁሉ እንደ ትንግርት እያዩዋት ስትጠየቅ ሰነበተች ።

የማስታወስና የመገንዘብ ችሎታዋ ከተመለሰ በኋላ በቂ ቆይታ በሀኪም ቤቱ ውስጥ ስላደረገች ፤ የአካል ቁመናዋ በመደርጀቱም ከመኝታ ተነስታ በግቢው ውስጥ እንደልብ በመንቀሳቀስዋ ከቤተሰብዋ ተቀላቅላ መኖር

እንደምትችል ሀኪሞቹ ስላረጋገጡ የመውጫዋ ቀን ተነገረ ። በሀኪሞቹ ምክር መሠረት ከወትሮው የተለየ በምታየውና በምትኖርበት ሁኔታ ላይ ሰላም ደስታ ሊሰጣት የሚችል አዲስ አካባቢ መፈለግ እንዳለበት በመረዳት ስለማረፊያዋና ስለ ወደፊት የአኗኗሯ ሁኔታ ምክር ሊደረግ ተወሰነ ።

በተለያዩ ምክንያቶች የነበረችበት የአቶ ተገኑ ቤትና አፍንጮ በር አፋፍ ላይ ካሉት መንደሮች መካከል የተሸጐጠችው የእናቷ የወ/ሮ ሙሉም ቤት ለማረፊያዋ ሳይመረጡ ቀረና ከሆስፒታል እንደ ወጣች በቀጥታ ወደ ሲስተር ፋናዬ ቤት እንድትገባ ሆኖ ስምምነት ተደረገ ። ይህ ስምምነት በይበልጥ የተደገፈው ከዕለት ዕለት የጤናዋን ሁኔታ ባላት ሙያ ሳቢያ መከታተል የምትችለው ሲስተር ፋናዬ በመሆኗ ይህንም በማገናዘብ ጭምር ነበር ። የቤት ሰቡን ጥያቄ በሙሉ ፈቃደኝነት የተቀበለችው ሲስተር ፋናዬም የሚገባውን ቅድመ ዝግጅት ከመኩሪያ ጋር ሲያደርጉ ቆይተው በዕለተ ሐሙስ ታጅባ ከሆስፒታል ወጣች ። በመኩሪያና በመቶ አለቃ አፈወርቅ መኪና ውስጥ ኋላና ፊት ሆነው እየተሳሳቁ እያወሩ ከሚመጡት መካከል ቅሬታ መንፈሱን የወጋው አሰግዴ ወርቁን ብቻ ነበር ። መራቅዋን አልወደደውም ። ወደ ሲስተር ፋናዬ ቤት በተቃረቡ ቁጥር አካባቢውን ቀደም ብላ እንደምታውቀው እየተደነቀች ልትናገር ያሰፈሰፈችውን ውዴን ወ/ ሙሉ በቁጣ ግልምጫ ዐይኖቻቸውን ስላሳረፉባት መልሳ ውጣ ዝም አለች ። ከቦታው ደርሰው አብሯቸው የመጣውን ልብስና እቃ እያንጠለጠሉ ወደ ቤት ሲገቡ ወ/ሮ ሙሉ ወደ ኋላ ቀረት ብለው ውዴን ጠርተው በሹክሹክታ አነጋገር ማስጠንቀቂያነት ያለው ቃል ሲነግሯት ደጋግማ በእሺታ ተቀበለቻቸው ።

ምዕራፍ ስድስት

ማታ ከሁለት ሰዓት ጀምሮ የሚካሄደው ስብሰባ ጉዳይ ሰላም ሊሰጠው አልቻለም ። በርካታ ነዋሪዎች የሚገኙበትን ሰፈ መንደራቸውን በማኅበራዊ ኑሮ ወግና ሥርዓት ለማደራጀት በማሰብ ለጥበቃውም ፤ በሞት አደጋ ወቅት ለሚደርሰው ችግር መልክ ባለው ሁኔታ መረዳዳት እንዲቻል የሚያስተባብር ኮሚቴ ለማቋቋም ጥቂት በጐ አሳቢ ነዋሪዎች መልእክትና ጥሪ ባስተላለፉት መሠረት እሱም ጥሪው ደርሶት በሀሳቡም አምኖበት ተሰብስቦ ነበር ። በስብሰባው ላይ አስተያየት በመሰንዘር ሀሳብ በማመንጨት ባሳየው ተዋህዶ ኮሚቴውን አዋቅረው ውጤት ያለው ሥራ ይሰራሉ ተብለው ከተመረጡት ሰዎች መካከል ውብሸት እንዳይላሉም አንዱ ሆነ ። ጥሪውም ግቡን መታና የተፈለገው ዕድር መሠረቱ ተጣለ ።

በዕለቱ ምርጫውንም ያለ ቅሬታና መግደርደር ተቀብሏል ። ከምርጫው በኋላ ግን ሰላም አጥቶ ሰነበተ ። አዳሩንም የረባ እንቅልፍ ሊወስደው አልቻለም ። በሰብሳቢነቱ አዲስ የተመረጡትን የኮሚቴ አባላት አሰባስቦ የአካባቢውን ነዋሪ የሚተዳደርበትን ሕግና ደንብ ለመንደፍ እያንዳንዱ ሰው በግሉ የሚወጣውን ኃላፊነት የሚከፋፈልበት የሥራ ድርሻ ድልድል ለማድረግ ልዩ ልዩ ዕቅዶችና መንደርደሪያ ሀሳቦችን አሰናድቷል ። ብቻ ስብሰባውን ተጨነቀበት ። ጭራሽ ከዕድር ሰብሳቢነቱ ራሱን

ሊያወርድ አሰኘው ፤ ሆኖም ይሉኝታ አሸነፈውና የግድ ዕድሩን ሊመራ ተጠናከረ ። ማታ ስለሚደረገው ስብሰባ እያሰላሰለ ጥዋት ወደ ቢሮው ስለገባ ሥራውን በረጋ ሁኔታ ሊያከናውን አቃተው ። እንዲፈርምበት ከፊቱ የተዘረጋውን ደብዳቤ ዐይኖቹ ደጋግመው ሲመለከቱት ቢቆዩም አላስተዋለም ነበርና ቁም ነገሩ አልታወቀውም ። ደንቃራ የሆነበትን ሀሳብ ከጭንቅላቱ በንቅናቄ የወጣው ይመስል ራሱን መላልሶ ካወዛወዘ በኋላ የረጅም አፍንጫውን ጫፍ በሁለት ጣቶቹ እያሻሸ ከተቀመጠበት ተነስቶ የቢሮውን መስኮት ወለል አድርጐ ከፈተው ።

ማዶውን ከርቀት የሚታየው የመቃብር ሀውልትና ሥፍራ አቀማመጡ ፤ እቅዱ ለማያውቀው የመናፈሻ ቦታ ይመስላል ። የዕብነ በረዱ ንጣት ፤ የጥዱ የቁልቋሉ ።የሣሩ ለምለምነት ፤ የተራቆተው መሬት ቡናማነት ተጋግዘው ማራኪ ህብረ ቀለም ፈጥረው ይታያሉ ። ሥፍራው የኑ በሩና የሌሉ ሰዎች ማረፊያ መካነ መቃብር በመሆኑ ዘወትር ዐይኑ ተወርውሮ ቅሬታን ቆንጥሮ የሚመለስበት ነበር ። በዚያን ጊዜ ሁኔታው ግን አሻግሮ እያየ ሙታንና መቃብሩን በአንክሮ ስላላስተዋላቸው ሥፍራው የሚፈጥርበት የዘወትር ስሜት ቀርቶ አእምሮው ውስጥ የሚተራመሰው ሀሳብ በተከለበት ጭንቅ ተመስጧል ። እንደገና ጀርባውን በርቀት ላሉት የመቃብር ሀውልቶች ሰጥቶ ፊቱን ወደ ቢሮው መልሶ ጉድፍ የሌለበት አፍንጫውን እየዳበሰ ተለጥጦ ቆመ ። ዓላማ አልባ ከወዲያ ወዲህ ፤ ከላይ ወደታች የሚመላለሱት ዐይኖቹ በወዛም ገንቦ ላይ ተተክሎ በበቀለ የቤት ውስጥ አበባ ላይ አረፉ ።

መቼውንም ውብሸት እንዳይላሉ ውበት ያደንቃል ሴትና አበባ ይወዳል ። ሴቶች ሲሽኮረመሙ ሲቅበጠበጡ

ሲያስመስሉ ሲዋሹ ሲያለቅሱ በፍቅር ሲነዱ ማየት ያረካዋል ። ወዝና ሕይወት ያለው አበባ ከፊቱ እንዲጠፋም አይፈልግም ። አንገቱ ረጅም በሆነችው ብርሌ ላይ የተቀመጠችውን ቀይ ጽጌረዳ መለስ ብሎ አይቶ ፈገግ አለላት።

ጸሐፊው ጽጌ ቅጠላ ቅጠል በየጣሳው በየማሰሮው እያጸደቀች ቢሮውንና ቢሮዋን የአትክልት ሱቅ አስመስላዋለች ። የመሥሪያ ቤቱ ጸሐፍት ሴቶችም ውድድር የገቡ ይመስል በየቢሮአቸውና በየአለቃቸው ቢሮ በጣሳ በቢልቃጥና በምንቸት የተከሉት የአበባና የቅጠል ዓይነት በርካታ ነው ። የጽጌ ቢሮ ግን መላ ወደ ማጣት ተቃርቧል ።

በቀጠሮ ተሸኝተው የውሣኔ ወረቀታቸውን ሊወስዱ የመጡት ባለ ጉዳይ ተሸቆጥቁጠው እጅ ነስተው የተሻሸች ኮፍያቸውን በሁለት እጃቸው ይዘው በሩን መለስ አድርገው ሲቆሙ ጽጌ ለመናገር አልቻለችም ነበርና እንዲቀመጡ በእጅ ምልክት ወንበር አሳየቻቸው ። ባለጉዳይም በትህትና ዝቅ ብለው ከበሩ አጠገብ ባለው ወንበር ላይ አረፍ አሉ ።

ስትሰናዳ ነበር የገቡት ። አፏን እየከፈተች ግራና ቀኝ ከንፈሯን እየለጠጠች ቀለሙን ደጋግማ ላይ ታች ከናፍርዋን ቀባችው ። ቀጥላም ዐይኖችዋን መኳል ጀመረች ። ቅንድብዋንና ሽፋልዋን ሳይቀር በተለያዩ ቀለማት ዳሰሰችው ። ይህን እንዳበቃች በጆሮዋና በብብቷ ሥር ጥሩ መዓዛ ያለው ሽታ ረጭታ ተጠናቀቀች ክፍሉ በሚጣፍጥ ጠረን ተሞላ ።

ተደላድላ ከጽሕፈት መኪናዋ ፊት ለፊት ለመሰየም ስትመቻች ሌላይቱ ጸሐፊ ከሌላ ቢሮ መጥታ የጠዋት ሰላ

ምታ ተሰጣጡ ። በከንፈራቸው ሳይሆን ጉንጫቸውን እያስታከኩ ተሳሳሙ ።

" ውይ ዛሬ ሽክ ብለሻል "

" አንቺም ፐስ ብለሻል ፤ ብቻ ጉትቻሽ ከልብስሽ ጋር አልሄደም "

" ስሚ ፤ ትላንት የሰራሁት የሰንበት አድቬንቸር ፤ ሰውየውን ግንብ አስጠግቼው ጠፋሁበት ፤"

' ጫማሽ ከሮም መሆን አለበት "

የመሳሰለውን ዘመናውያኑ ሴቶች የተለዋወጡዋቸውን የሰኞ ማለዳ ጭውውት አገጫቸውን በእጃቸው አስደግፈው በዝምታ ያዳምጡ የነበሩት ባለ ጉዳይ ለቸኮሉበት ነገራቸው መልስ ስለ ፈለጉ ፤

" እባክሽ እህቴ ወረቀቴ ተፈርሞ ከሆነ ጠይቀሽ ብታሰናብቺኝ " ብለው ከቅምጣቸው ተነስተው ሲቆሙ ሰው በክፍሉ ውስጥ መኖሩ ትዝ ያላቸው ጸሐፊዎች ተያይተው ተሳሳቁ ። ከፊሉ እንግሊዝኛ ኩፊሉ አማርኛ በሆነ ቋንቋ ተነጋግረው በሻይ ሰዓት ሊገናኙ ተቀጣጥረው የመጣችው ወጣች ።

ጽጌ የደረበችውን ኮት ከወንበሯ ላይ አስተካክላ አስቀምጣ ወደ አለቃዋ ክፍል ተራመደች ። በዝግታ በሩን አንኳኩታ ከፍታ ገባች ። ኮፍያቸውን በጣቶቻቸው እያሻሹ የቆሙት ባለ ጉዳይ የመጡበትን ጊዜ አስበው ከጉዳያቸው አጣዳፊነት ጋር እያገናዘቡ በየቢሮው እርግጠኛው የሥራ መጀመሪያ ሰዓት ስንት ይሆን የሚለውንም ትዝብት ያሰላስሉ ነበር ።

በሩን ከፍታ ብቅ ስትል ሀሳቡንም ትዝብቱንም ጥለው ባለ ጉዳይ ቀና አሉ ። ጽጌ ከአለቃዋ ቢሮ አንጠልጥላው የወጣች ወረቀት አልነበረም ።

" አልተፈረመም ማክሰኞ ይመለሱ " አለቻቸው አንገቷን ሰብቃ

" እንዴት " አሉ በድንጋጤ ወዲያውም መበሳጨታቸው በደም ሥሮቻቸው መወጠርና መፍጠጥ እየታየ ፤

ጽጌም ትከሻዋን ከፍና ዝቅ አድርጋ ምን አውቃለሁ ዓይነት መልስ ሰጠቻቸው ።

ነጠቅ ነጠቅ ብለው ተራምደው አልፈዋት ወደ ውብሸት እንዳይላሉ ቢሮ ገቡ ። በሩን ጋርዳ ለመዝጋትም ይሁን ሰውየውን ጐትታ ለመመለስ ብቻ ሞክር ያደረገችው እንቅስቃሴ ሊያግዳቸው አልቻለም ። በሩን ዘግተው ለብዙ ደቂቃ ንግግሩ በውል ባይሰማም ጐላ ባለና በኃይል ቃል ሲነጋገሩ ቆይተው ደብዳቤያቸውን አንጠልጥለው ወጡ ። ባለ ጉዳይ ሲወጡ ጽጌን አልተሰናበቷትም ።

ውብሸት እንዳይላሉ ፤ ስለማታው ስብሰባ ጉዳይ ሲያነሳ ሲጥል ቆይቶ ህሊናውን ያመነበትን ይሻላል ብሎ የመረጠውን ሁኔታ ሁሉ ሊፈጽም ወስኖ ለጊዜው ላያስብ ተወው ። መንደርደርያ ይሆኑኛል ያላቸውን ነጥቦች በቅደም ተከተል የጻፈበትን ወረቀት እንደገና በንባብ ከወጣው በኋላ ከወረቀት መያዣው ቦርሳ ውስጥ ከተተው ።

ጭራሽ ከሰዓት በኋላ ሀሳብ ተደራርቦበት አንዱ ሌላውን እየቀሰቀሰ ፤ የራቀው የተዳፈነው ሀሳብ ሁሉ እየተቀጣጠለ እየተጥመለመለ በዓይነ ህሊናው እየተጋረጠ ስላስቸገረው ቢሮውንም ስላስጠላው ከሥራ መውጫ

ሰዓት ቀደም ብሎ ወጥቶ የስድስት ኪሎን ሀውልት ጫፍ ከርቀት እያየ ቁልቁለቱን እያሽኮረከረ ወረደ ።

መኪናውን ከመንገድ ዳር አቁሞ ከጆሊ ባር በረንዳ ተቀምጦ ቡና አዘዘ ። የቀረበለትን ቡና በማንኪያ እያማሰለ አሻግሮ አራት ኪሎ ሀውልት ጫፍ አምስት ሰዓት ብሎ በቆመው ሰዓት ላይ አፍጥጦ ሳይወድ ባሳለፈው የምርጫ ዕለት ሁኔታ ላይ ተመለሰ ። እካሌ ዳኛ ፤ እከሌም/ ዳኛ እከሌ ጸሐፊ እከሌ ገንዘብ ያዥ እከሌ ሂሣብ ሹም፤ እከሌ አባል እየተባለ በተራ በተራ ሲመረጥ ከዚያ መሀል ስሟ ተጠርቶ ብድግ ስትል አንዳች ነገር ለቅጽበት ነፍሱን የነጠቀው ያህል በድንጋጤ ደንዞና በድኖ ያየውንና የሰማውን ማመን አቅቶት ነበር ። ምንተስኖት ወልዱ የኮሚቴው ጸሐፊ ሆና ስትመረጥ በአካባቢው ያሉ ሰዎች ሞቅ ያለ ጭብጨባ አሰምተዋል ። ምን ተአምር ጐትቶ አምጥቶ ጐረቤቱ እንዳደረጋት መላ ሊመታ እንኳ አቃተው በዕለቱ የአጋጣሚውን መሰሪነት ስብሰባው ከመበተኑ በፊት ጀምሮ ማማረር ጀመረ። በምን ሁኔታ የሁለት ዓመት ዕድሜ ባለው ኮሚቴ ውስጥ እንደሚሰሩ እያሰበ ሳይወጠን ዘገነነው ። ምንተስኖት ወልዱን በሚገባ ያውቃታል ። እንደሾህ ፈራት ጉርብትናዋ ቀፈፈው ።

ምርጫው ተጠናቆ በኮሚቴው ውስጥ የሚሰሩት አባላት በቅድሚያ መተዋወቅ እንዳለባቸው ያመነው አስመራጭ ኮሚቴ አንዱን ከሌላው እያጨባበጠ ሲያገናኛቸው " ውብሸት እንዳይላሉ " እባላለሁ ብሎ እጁን ዘርግቶላታል ። እሷም " ምንተስኖት ወልዱ " ብላ አጸፋውን መልሳለት ነበር ። ጠበቅ ያለው አጨባበጧ የተወው አሻራ ያለ ይመስል ቡናውን ፉት ሳይል እጁን እንደገና አየው ። ነገር ሲያፍተለትል የቀረበለትን ቡና ሳይጠጣው በመቆየቱ ቀዝቅዞ በደነ ። እንደገና ሌላ

ትኩስ ቡና አዘዘና በትኩሱ ጠጥቶ የእርካታ ስሜት ሲያገኝ የሁለት ሲኒ ቡና ሂሣብ ከፍሎ ተነሣ ። ሚስቱን የሚቀበልበት ሰዓት በመድረሱ መኪናውን በእርጋታ እያሽከረከረ ወደ መኖሪያው ወደ ሾላ መስመር አቀና ። አበባየሁን ከዋናው መስመር ላይ የሚጥላት የመሥሪያ ቤቷ የመመላለሻ አገልግሎት መኪና እንደ ቆመ ደረሰ ። ወረድ ብላ ውስጥ ላሉት የመ/ቤቷ ባልደረቦች በቄንጥ ጣቶችዋን ለስንብት ካንቀሳቀሰች በኋላ ባለቤቷ ወደ ቆመበት የመንገድ ዳርቻ ተራመደች ። ከወለደች በኋላ ጥቂት ክብደት የደረበች ቢሆንም ቅርጽዋ አልተበላሸም ። የቅላትዋ ድምቀት ጨምሯል ። የፊትዋ ሥጋ በመጨመሩም ዐይኖቿ ከመቼውም አንሰው ይታያሉ ። አረማመድዋን፤ ትክለ ቁመናዋን እንገደገና በአንክሮ እየተመለከተ ተደሰተበት ። የመኪናውን በር ከፍታ ሰላምታ ሰጥታው ከጐኑ ከተቀመጠች በኋላ ወደ ቤታቸው በዝግታ ወረዱ ።

ውብሸት እንዳይላሉም ሆነ አበባየሁ ህሊናቸው ሲጐተትበት ቀልባቸው ሲንጠለጠልበት የሚውለውን የልጃቸውን ናፍቆት ለመወጣት ከሥራ ወደ ቤት የሚገቡበትን ሰዓት ይወዱታል ። በጥሩ እንክብካቤ የተያዘችው ልጃቸው ፈጣን እድገት እያሳየች በመሆኗ የትም የትም ያያት ሁሉ ይሳሳላታል ። መልኳና ቀ ለሟ ወደ እናቷ ያደላው ልጃቸው ግን ውሎዋ ከሞግዚቷ ጋር በመሆኑና እሷን በመልመዷ ለወላጆቿ እምብዛም ግድ የላትም ። ከሥራ መልስ ለማታ ትምህርት ስትል ሞግዚትዋ ስትለያት መነጫነጭና ማልቀስ ልማዷ ነው ። በዚህ ወቅት ሕጻኗን በጋሪው ላይ ጭኖ በበረንዳው ላይ ከወዲያ ወዲህ እየጐተተ እያሽከረከረ ያባብላታል ያጨዋውታታል ። እንደ ገቡ ንጹህ ልብሷን አለባብሳ ምግቧን መግባ ሕጻኗን ስታመጣት እንደ ልማዳ ከሞግዚቷ ላለመለየት አለቀሰች ።

ለቅሶዋን ለማቆም እያጨዋወታትም ለማባበል ሲል ያደርግ እንደነበረው ማንሸራሸሩን አልፈቀደውም ። ህሊናው ውስጥ የተጋረጠው ሀሳብ ስላወከው የመጨነቅ የመቅበጥበጥ ስሜት ወሮታል ። ለስብሰባው የተወሰነው ሰዓት አርባ ደቂቃዎች እንደ ቀሩት ካረጋገጠ በኋላ መታጠቢያ ክፍል ገብቶ ተጸዳድቶ በቀዝቃዛ ውሀ ፊቱን ታጥቦ ወጣ ። ወፍራም ጋቢውን በቁመቱ ሙሉ ተጐናጥፎ ሲነሳ ሁኔታው የገረማት ሚስቱ የት እንደሚሄድ ጠየቀችው ። የኮሚቴው የመጀመሪያ ስብሰባ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ላይ እንደሚካሄድ ነግሮአት ወረቀቶቹን ጨብጦ ወጣ ።

የግቢው ነዋሪ በተሰበሰበበት ዕለት ኮሚቴውን መርጦ ሲጨርስ የተመረጡት አባላት ደግሞ የመጀመሪያውን መሰብሰቢያ ቀንና ቦታ ሲወስኑ በጸሐፊዋ በምንተስኖት ቤት እንዲሆን በመምረጣቸው በተባለው ሰዓት በቦታው ለመገኘት እያዘገመ ወደ ታች ወደ ቤቱ አቅጣጫ ወረደ ።

ከተመራጮች አንዱ ወደ መሰብሰቢያው ቤት ሲሄድ ስላገኘው ደስ ብሎት እየተነጋገሩ ከምንተስኖት መኖሪያ ደረሱ ። በሩ ሲከፈት ፈገግታ ባለው ሰላምታ ተቀበለቻቸው ። ቀድመው የገቡትም ሁለት ሰዎች ቆመው ተቀብሏቸው ። ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ በምክትል ሊቀ ዳኝነት የተመረጠው ሰው በመቅረቱ ጥቂት ጊዜ ሊጠብቁት ተስማምተው ባሰባሰባቸው ጉዳይ ላይ መወያየት መጨዋወት ያዙ ።

ቀፎ ቀራጭ ይመስል እስከ ቅንድቡ የተሸፋፈነው ውብሸት እንዳይላሉ በውስጡ የሚተራመሰው ሀሳብና ጋቢው በፈጠረበት ሙቀት የተነሣ ፊቱ በላብ ወዝቶ ብዙውን ጊዜ ዐይኖቹ በያዘው ወረቀት ላይ ብቻ ተወስ

CamScanner

ነው አልፎ አልፎ ግን በቴሌቢዥን ላይ ወዳለው የልጅ ፎቶግራፍ ብቻ ይወረወራሉ ።

እንደ ሌሎቹም ሁሉ ምንተስኖት ጆሮዋን አቅንታ የሰው ድምጽ ወይም ኮቴ ትጠብቃለች ። ምንቴ የምትጠብቀው ግን የተመረጠውን የኮሚቴ አባል ብቻ ሳይሆን የሲስተር ፋናዬንም መምጣት ነበር ። አለወትሮዋ ስላመሸችባት ልቧ ተሰቅሏል ። ከአስራ አምስት ደቂቃ ቆይታ በኋላ በሩ ሲንኳኳ በሩን ለመክፈት ስትሄድ በመጠበቅ ላይ ያሉት አባላትም ለስብሰባው መጀመር እርግጠኞች ሆነው ብዕርና ወረቀታቸውን እያሰናዱ ካቀማመጣቸው ተስተካክሉ ። እየተሳሳቁ የገቡት ግን ፋናዬ ውዴና መኩሪያ ነበሩ ።

ከውጭ የገቡት ሰዎች የሰዎቹን መሰባሰብ አይተው በመደንገጥ ፤ በቤቱ ውስጥ የነበሩት ደግሞ የጠበቁት ቀርቶ ሌሎች በመምጣታቸው የተደነቁ መስለው ተያዩ ምንቴም የፋናዬን እንጂ የውዴንና የመኩሪያን መምጣት ስላልጠበቀችው ግር ብሏት ነበር።ወዲያው ራሷን አሰባስባ ተከታትለው የገቡትን ሰዎችዋን ከኮሚቴው ተመራጮች ጋር አስተዋወቀች ። አባላቱ ከተቀመጡበት እየተነሱ በመጨበጥ ሰላምታ ሰጧቸው ። መጀመሪያ ውዴን ቀጥሎም መኩሪያን ሲያይ እጁ ብዕር መጨበጥ የተሳነው ውብሸት እንዳይላሉ በጋቢው ውስጥ አካሉ መንቀጥቀጥ ጀምሯል ። ለአጭር ጊዜ የሚቆይ የኮሚቴ ስብሰባ እንዳላት በመግለጽ አመሻሽተው እንዲመጡ እና ሲስተርን ከይቅርታ ጋር ከሸኘች በኋላ ወንበርዋን ስባ ተደላድላ ስትቀመጥ መኩሪያን በልጅዋ አጐትነት ፋናዬን በጓደኝነትዋ፤ ውዴን ልጅዋ እንደሆነች የዝምድናቸውን ደረጃ ጭምር ለኮሚቴው አባላት ገለጸችላቸው ።

ውዴ ግን እንደ ቀድሞው ለጥ ብላ እጅ ለመንሣት ሞክራ ባይመቻትም ትህትናና አክብሮት የተሞላው ሰላምታ ከሰዎቹ ሁሉ አብልጣ ለውብሸት እንዳይላሉ ስሙን ጠርታ ስታቀርብለት አጸፋውን ሊመልስላት አልቻለም ። ይህም ውዴን እየገረማት ሄዳለች ውዴ ቀደም ሲል ወ/ሮ ሙሉ በሰጧት ማስጠንቀቂያ መሠረት ስለውብሸት ዕውቀት አልተናገረችም ። የመኩሪያ መኪና ድምፅ ሲርቅ ለተፈጠረው የጊዜ መባከን ምንተስኖት ይቅርታ ጠይቃ የስብሰ ባውን ቃለ ጉባኤ ለመያዝ ብዕሯን ጨብጣ ተዘጋጀች።

አካላቸውንና መንፈሳቸውን አሰባስበው በም/ ዳኛውም መቅረት አምነው በምሽቱ በሚያነሷቸው ጉዳዮች ላይ ለመነጋገር የተዘጋጁት አባላት ንግግራቸውን ገትተው የዳኛውን ድምጽ ለመስማት ጠበቁ ። ውብሸት እንዳይላሉ አንገቱን እንደ ማቀርቀር አድርጐ ዐይኖቹ በጽሁፉ ላይ አትኩረው ይታያሉ ። አጠገቡ ያሉት አባል ስሙን ጠርተው ስብሰባውን እንዲጀምር ሲያሳስቡት ወዲያውም ትክሻውን ነካ አደረጉት ። ግንባሩ ከጠረጴዛው ጋር ሲጋጭና ከተቀመጠበት ወንበር ላይ ዘምበል ሲል ከጐኑ የነበሩት አባል ፈጥነው ያዙት ። የተቀመጡት ሁሉ ተደናግጠው ተነስተው ገሚሱ የተጐናጠፈውን ጋቢ ለመግለጥና አየር እንዲያገኝ ሲተጋገዙ ሌሎቹ ደግሞ ምንተስኖት ፈጥና ካመጣችው ቀዝቃዛ ውሀ በመሀረማቸው እየነከሩ በግንባሩ በማጅራቱና በደረቱ ላይ አፈሰሱለት ። በአፉ ደም መምጣቱን ሲያዩ ተሯሩጠው የጐረቤት የመኪና እርዳታ ጠይቀው ሚስቲቱንም ጠርተው ወደ ሆስፒታል ተወሰደ ። ከኮሚቴ አባላት መካከል ሁለቱ ደግፈውት ሲሄዱ ሌሎቹ ከመኪናው መሄድ በኋላ በደረሰው ድንገተኛ ሁኔታ አዝነውና ደንግጠው

እንደ ተሰባሰቡ ከመንገዱ ዳር ብዙ ጊዜ ቆሙ ። የደም ብዛቱ (ግፊቱ) እጅግ ከፍ ብሎ ነበር ።

ስብሰባቸውን ላልታወቀ ጊዜ አስተላልፍው ሁሉም ወደ የቤታቸው ሲመለሱ ምን ተስኖት የነበረችበት ስሜት የተመሰቃቀለና በጭንቀት የተወጠረ ነበር ። እርካታ ወይም አዘኔታ መሆኑን በውል ለይታ ልታውቀው አል ቻለችም ። ተመልሳ በቆመችበት በረንዳ ላይ ፈዝዛ ሁኔ ታውን ሁሉ በዓይነ ህሊናዋ እንደገና እያየች በሀሳብዋ ውስጥ ሰምጣ ነበርና የነመኩሪያን ተመልሶ መምጣት እንኳን አልተመለከተችም ። ከመኪና ወርደው እየተነ ጋገሩ ሲመጡ የመናገር ቀርቶ የመንቀሳቀስ ምልክት ስላላሳየቻቸው ጤናዋን በመጠራጠር ፋናዬና መኩሪያ በግራና በቀኝ አቅፈው ዳበሷት ጠያየቋት ። ወደቤት ይዘ ዋት ሲገቡ የወንበሩን መመሰቃቀል የወረቀቶቹን መበ ተን አይተው በነገሩ ግራ የተጋቡት ፋናዬና መኩሪያ ምን ችግር እንደ ተፈጠረ አጥብቀው ጠየቋት ። ከውብሸት እንዳይላሉ እጅ ተንሸራታ የወደቀችውን ብዕር ከመሬት አንስታ በወረቀት ላይ መስመሮችን በዝግታ እያጋደመች የሆነውን ሁሉ በርጋታ ነገረቻቸው ።

የደነገጠችውና አስቀድሞ እንባዋ የፈሰሰው ፤ ውዴ እናቷ ወ/ሮ ሙሉ የጣሉባትን ማስጠንቀቂያ ጥሳ በው ሸት እንዳይላሉ ቤት ግማሽ ቀን ስትሰራ በአዘኔታ እንዳ ያት እርዳታም ያደርግላት እንደነበር እያወሳች ዜማ ያለው ለቅሶ አለቀሰች ። በቁጣም በማባበልም ዝም ካሰ ኙዋት በኋላ ሁሉም በመደነቅ በቤቱ ሠራተኛ ሆና ያሳለ ፈችውን ጊዜና ሁኔታ እንድትነግራቸው ሶስቱም በርካታ ጥያቄዎችን ሲያቀርቡላት አመሹ ። በሆነውና ይልቁንም በሰሙት በአጋጣሚውም ውጤት ተነክተው ሁሉም በያ ሉበት ተክዘው ያለ ንግግር ረጅም ጊዜ ቆዩ ።

ከቴሌቪዥኑ ትይዩ በተዘረጋላት አልጋዋ ላይ ጋደም ብላ ዐይኖቿዋን በሰፊው ከፍታ ጣራውን አሻቅባ እያየች አልፎ አልፎ እንባዋን ኵለል ስታደርገው ምንቴን ለማጽ ናናት ወይም ለማስተው አንዳቸውም አልሞከሩም ።ፋና ዬም ብትሆን የምንተስኖትን ሕይወት ቀደም አድርጋ ከመኩሪያ የሰማች በመሆኑ ይህ አጋጣሚ የፈጠረውን ሁኔታ እየገረማት በማሰላሰል በከባድ ሀሳብ ተውጣ ነበር። መኩሪያም የውዴን ጭንቅላት ከጭኑ ላይ አስደግፎ ጸጉ ሯን እያሻሸ እጅግ በጠለቀ ትካዜ ልቡ ተሰብሮ ምስቅል ቅል ባለ ስሜት ነገር ያሰላስል ነበር ።

CamScanner